ታጠቅ

ዓለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ሕብረት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

P.O.Box 3198, 10364 Stockholm,3
SWEDEN

"የካፒታሊስት አልባ ዕድገት"

ሐምሌ 1973

በሳም ውድ ጓዶች ፣

እነሆ ባለኝ አቅምና ችሎታ ስለ ካፒታሊስት አሰባ አዴገት ቲያትር አንዱ ጥናት አቀናብሬ ልከሰሰሁ:: እንደምትመለከቱት ጽሁፉ መበረታቻ ነገሮችን ያዘለ ነው:: ተቀብቹ በእኔ ግምት በዝቅተኛው ቦታ የገቡ ይመስለኛል::

ሆኖም ግን ጽሁፉ አንዳንድ ነገሮችን አሳጥሎም የሚትሉ ከሆነ እናንተ ልታሟሉት ትችላላችሁ:: ወይንም ደግሞ እናንተው አረባችሁ እንደፈረደባችሁ ጊዜያችሁን በማቃጠል አማርኛውን በማስተካከል ቀደም ተከተሉን በማባመር በታወጡት ጥሩ ነው:: እንደዚህ ስል ግን በፊቤ ላይ እምነት የለኝም በቄ ባይሆን፣ እንደምታውቁት አንዱ ሆና ከበራት ሁለት በስት ሆነው የበሬት ጥሬት ይኖረ ግል ከሚል እምነት የተነሳ ነው::

የናንተው
ዓለሙ ወልደ/ጊዮስ

መቅድም

በማንኛውም አገባር ቢሆን፣ የቲያትር ጥናቶችን ማበረታታ አስፈላጊ ነው:: ለአንዱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የቲያትር ውይይቶችንም ማበረታት እንደዚሁ አስፈላጊ ነው:: ይህ የአጥቂትና የትገል መስክ፣ አስተያየቶችን ያንፃል፣ ንቃተ ህሊናን ያዳብራል፣ አመለካከቶችን ያጋርነት ባህርይ ይበዛቸዋል፣ አእምሮን ያለመልማል::

ዓለሙ ወ/ጊዮስ የተባለው ጓድ፣ ስለ ካፒታሊስት አሰባ አዴገት፣ እርበው አባሪ አዋርግ በላኩው ደብዳቤ ውስጥ እንዳለው፣ 'ባለው አቅምና ችሎታ አቀነባበር' አቅርቧል:: ስሁፉን የተጋላ ነው ብሎ፣ ደረቤው የማያምነውን ያህል፣ እኛም፣ ገና ብዙ ጥናትና ውይይት የሚደረግበት ርእስ ነው ብለን እናምናለን:: ለምሳሌም ያህል፣ በኢኮኖሚው ጥያቄ ረገድ ብዙ ጥያቄዎችን ማቀረብና መመርመር አስፈላጊ ነበር:: ሁለተኛም፣ የአንዳንድ አገሮችን ልምምዱና ያመራበትን አቅጣጫ ሆነ የሚገኙበትን ሁኔታ እንደ ምሳሌ እየወሰዱ በዝርዝር ማቀረብ ያስፈልግ ነበር:: በዚህም አገባር፣ ኀብዶን፣ ኢራክን፣ በርማን፣ በማሊን፣ ... ወዘተ. ለመመልከት ይቻል ነበር:: እንደዚሁም፣ የዛሬይቱ የሃገራችን ሁኔታ አለ:: የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታቸውን በራሳቸው አዱራጊነትና መሪነት ይመሩበት የነበረበት ዘመንና /1966 -1969/ ሶቪየት ህብረትና ተጠሳያጆ ገብተው መፈትፈት ከጀመሩበት ወቀት ወዲህ ያለው ዘመን /ከመጋቢት ሚያዝያ 1969 ጀምሮ/ በባህርይም በተፈጥሮም አንዱ አይደለም:: ... ወዘተ.

የሆነው ይሁንና፣ ጓዱ 'ባለው አቅምና ችሎታ' ያቀረበው ጽሁፍ፣ ሌሎችን ለበለጠ ጥናትና ምርምር እንደሚያነሳሳቸው እንተማመናለን:: ይህንኑ በማስረገጥና ሌሎችም፣ ተመሳሳይና ሌሎች ጥናቶችን እንደ ጓዱ እየደረሱ እንዲያቀርቡ ጥሪያችንን በማደስ ለአንባቢያን 'ስለ ካፒታሊስት አሰባ አዴገት' የተባለውን የጓዱ ዓለሙ ወ/ ጊዮስን ጽሁፍ በዚች የታጠቅ አካም ውስጥ አቅርበናል:: መልክም ንባብ፣ መልክም ጥናት፣ መልክም ውይይት እያልን ቢሆንም፣ የመጽሄት ቦርዱ፣ በጓዱ ጽሁፍ ላይ ከንዳንድ ጥያቄን የያሳትና የሃረግ እርማቶች በስተቀር፣ ምንም አይነት ማሻሻያ ወይንም ለውጥ እንዳላደረገበት እንገልጻለን:: የጽሁፉ ተጠያቂና ሃላፊ፣ የጽሁፉ አቅራቢ የሆነው ጓዱ ዓለሙ ወ/ጊዮስ ነው::

የአኢተማ መጽሄት ቦርዱ

መግቢያ

ይህንን ጽሁፍ ለማዘጋጀት የተባበሩኝን አንባቢያንን ሙሉ በሙሉ አረካለሁ በሚል ግምት አይደለም።

ሆኖም ግን፣ አጠቃላይና መሰረታዊ የሆነ፣ በተጨማሪም ለማንም አንባቢ ግልጽ የሆኑ ሃሳቦችን ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንጻር እያወዳደርኩ፣ የቲዎሪውን ይዘት በመልክ በመልኩ ለማስቀመጥ በመሞከር ነው። ይህም ለወደፊት የሰፋ መስፋፋትና ሙሉ ትችት አንዱ መነሻ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

የተለያዩ በቦሸየት ቲዎሪቲሽን የተጻፉ ይህንን ቲዎሪ እንደአማራጭ አዱርገው የሚያቀርቡት፣ የቲዎሪ ውዥንብር ብቻ ያለው ባይሆን፣ በመሃከላቸው አለመግባባትና አንዲያውም በራሱ በአንዱ መጽሃፍ ውስጥ እርስበርሳቸው የሚጋጩ አቀራረቦች በመኖራቸው፣ አንደኛውን ትቶ ሌላውን መተቸት አስቸጋሪ በመሆኑ ለሁሉም ይዘት ጠቅም ያባቁል በሚል ግምት፣ በመሰረታዊ ነገሮች ላይ ብቻ በማተኮር፣ የቲዎሪውን ምንነት፣ ይዘትና ዓላማ አንባቢያን በማያስቸግርና ሸማቲ በሆነ መንገድ አቀርባለሁኝ። ይሁንና ስለዚህ ቲዎሪ በዙ መጽሃፍት ቢጻፉምና በመሃከላቸውም አለመግባባት ቢኖርም በመሃከላቸው አጠቃላይ ስምምነት አለ። የትችቱ መነሻ በእነዚህ አጠቃላይ ስምምነቶች ላይ የተመረኮዘ ይሆናል ማለት ነው።

ከዚህም በመነሳት የትችቱ የመጀመሪያው ክፍል የካፒታሊስት አልባን ቲዎሪ በታሪካዊ ቁስ አካል መነጽር መመርመር ይሆናል። በተጨማሪም በዚሁ ክፍል ንኡስ ክፍሎች የቲዎሪውን ፖለቲካዊ ሆነ ኢኮኖሚያዊ ይዘት ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንጻር መመርመር ይሆናል እንዲሁም ይህ ቲዎሪ ለምን ጎጂ እንደሆነና አሳማኝ እንደሆነ፣ በአንዱ አገር የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ሊያመጣ የሚችለውን አሉታዊ ውጤት ባጭር ባጭሩ አሳያለሁኝ።

በክፍል ሁለት፣ የአዲሱን ዲሞክራሲ አብዮት ታሪካዊ አመጣጥ አጠር ባለ መልክ ይቀርባል። በተጨማሪም የአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት ፖለቲካዊ ሆነ ኢኮኖሚያዊ ይዘት እንደዚሁ ሸማቲ በሆነ መልክ ይቀርባል።

ማውጫ

1.0 የካፒታሊስት አልባ እድገት/የካ.አ.እ/ ቲዎሪ ምንነትና ትርጉም....ገፅ 1

1.1 የካ.አ.እ በታሪክ ቁስ አካል መነፅር.......... 1

1.1.1 የካ.አ.እ ና የማርክስ እንገልስ አባባል.......... 3

1.1.1:1 የካ.አ.እ ቲዎሪና የሌኒን አቀራረብ.......... 5

1.2 የካ.አ.እ ና የኢኮኖሚ ይዘት.......... 7

1.3 የካ.አ.እ ና የፖለቲካ ይዘት.......... 9

1.3.1 ይካ.አ.እ መንግስት ምን ይመስላል?.......... 12

1.3.1.1 የካ.አ.እ በዴሞክራሲ ላይ ያለው አመለካከት.......... 13

1.3.1.1.1 የካ.አ.እ ቲዎሪና የሳዐሳይ መቀቀር ጉዳይ.......... 13

1.3.1.1.1.1 የካ.አ.እ የቦሸሲት ምርጫ ትንትበአረቭዎና በአብዮታዊ መንግስት መኪና ላይ በመመርኮዝ ለመገንባት ይቻላል ይላል።.......... 15

1.4 የካ.አ.እ ቲዎሪ 'ታሪክ ሠሪው በሬው ህዝብ ነው' የሚለውንና 'የበሬስ ላይ መተማመን'መሪከር አይቀበልም።.......... 17

1.5 የካ.አ.እ ኢሲስ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቲዎሪ ነው.......... 19

1.6 ማጠቃለያ.......... 23

2.0 የአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት ታሪካዊ አመጣጥ.......... 24

2.1 ሦስተኛ አገሮች ለምን በአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት ማለፍ አለባቸው.. 25

2.2 ሕዝቡ ዲሞክራሲ መንግስት.......... 27

2.3 የአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት ኢኮኖሚ 28

2.4 ማጠቃለያ.......... 29

1.0. የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪ መነሻና ትርጉም

1.1 የካፒታሊስት አልባ እድገት በታሪክ ቁስ አካል መነፅር

ይህ ሀረግ ቃል በቃል ሲተረጎም አንድ ህብረተሰብ ከአንደኛው ወደ ሌላኛው ለመሸጋገር፣በመሃከሉ የሚኖረውንና መኖር ያለበትን የእድገትን ደረጃ ሳይነካ በቀጥታ ሊሸጋገር ይችላል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ህብረተሰብ ከቅድመ ካፒታሊስት (pre- capitalist) ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር የካፒታሊስትን የእድገት ደረጃ ዘሎ ወደ ከፍተኛው የኢኮኖሚ ወይም የህብረፀሰብ ሥርዓት ውስጥ ሊገባ ይችላል ይላል፡፡ በዚህ ቲዎሪ አባባል፣

("..in the era of imperialism and socialist revolutions, the peoples of backward countries can achieve socialism not through capitalist development, but by passing it or interupting it in an early stage " (1)

"በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊስት አብዮቶች ዘመን፣ ወደኋላ የቀሩ አገሮች ህዝቦች ሶሻሊዝምን ሊቀዳጁ የሚችሉት በካፒታሊስት እድገት ሳይሆን፣ እርሱን በማለፍ ወይም በእንጭጩ እንዳለ በመቅጨት ነው፡፡/ ትርጉም የኛ /

የታሪክ ቁስ አካላዊነት ወይም የህብረተሰብ እድገት ህጋጋት የሚያስተምረን ምንድ ነው ?

የሰው ልጅ ባሳለፋቸው የህብረተሰብ እድገት ደረጃዎች፣ ሰዎች በዘፈቀደ ይህንን ወይም ያኛውን ስልተ ምርት ወይም የኢኮኖሚ ሥርዓት በመምረጥ አንደኛውን ዘለው ወደሌላኛው ሊሸጋገሩ አይችሉም፡፡ ከጥንታዊ ጋርዮሽ ወደባሪያ፣ ከባሪያ ወደ ፊውዳል፣ ከፊውዳል ወደ ካፒታሊስት፣ ከዚያም ወደ ከፍተኛው ሥርአት፣ ማለት ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር፣ በእያንዳንዱ የህብረተሰብ ሥርአት ውስጥ ለሚቀጥለው የምርት ግንኙነት የሚያገለግሉ፣ የማቴሪያል ሁኔታዎች ተጸንሰው መዳበር አለባቸው፡፡ እነዚህ በአሮጌው ህብረተሰብ ውስጥ /ለምሳሌ ከካፒታሊዝም በፊት በፊውዳሉ ሥርአት ውስጥ/ የተጸነሱት የማቴሪያል ሁኔታዎች ቀስ በቀስ በመዳበር ከአሮጌው የምርት ግንኙነት ጋር እየተቃረኑ በሀገገን ለጎን ለተወሰነ ዘመን ይኖራሉ፡፡ በተወሰነ የታሪክወቅት በአሮጌውና በአዲሱ የምርት ግንኙነት መካከል ቅራኔው ይከረል፡፡ አሮጌው በአዲሱ ቦታውን እንዲለቅ ይገደዳል፡፡

በይበልጥ ገለጽ ለማድረግ፣

ለምሳሌ በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ገና ለገና የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ መሰረት የሆኑ የማኑፋክቸሪ ኢንዱስትሪ መስፋፋትና ማደግ፣ ጪሰኛውና ገበሬ ተቀጥሮ ያርስበት የነበረውን መሬት እየለቀቀ ወደ ኢንዱስትሪ አምባዎች መምጣትና ወዘ. እያደር መሆን በሙሉ የበርዥዋው የኢኮኖሚ ግንኙነቶች፣ የፊውዳሉ ሥርዓት አንድ የእድገት ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ ተጸንሰው እድገው ወደፊት አብረው እየተቃረኑ መጓዝ ጀመሩ፡፡ ነገር ግን አዲሶቹ የምርት ሃይሎች /ወዘ እየደረ የኢንዱስትሪ መኪና፣ ወዘተ.. / ፈጣንና ታላቅ ስለ ነበሩና አሮጌው ጉታች በመሆኑ ተቻችለው ለብዙ ጊዜ አብረው መቀየት አይችሉም፡፡ በሁለቱ መሃከል የነበረው አለመጣጣም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቶ በአንድ የተወሰነ የታሪክ እድገት ሳይበቃረንዓት ለአዲስ የምርት ግንኙነት ቦታውን እንዲለቅ ተገደደ፡፡ እንደዚህ ነው በአጭሩ የህብረተሰብ የእድገት ጉዳና፡፡ በመሆኑም በአሮጌው የምርት ግንኙነት ውስጥ ለአዲሱ የሚሆኑ የማቴሪያል ሁኔታዎች ባይፈጠሩ ኖሮ፣ እያደዘም በመሃከላቸው እያደገ የሚመጣ ቅራኔ ባይኖር ኑሮ በመሃከላቸው ሊፈነዳ የሚችል ቅራኔ ባልኖረም ነበር፡፡

ወደ ሌላ አዲስ ስርአትም መሸጋገር ባልተቻለም ነበር፡፡ ነገር ግን የህብረተሰብ እድገት ታሪክ እንደሚያሳየን፣ ሰው የአሪሱን ኑሮ ከአለት አለት ለማሻሻል በሚያደርገው ትግል ባየወዉ በገዉ፣ ከሱ አእምሮ ጭምር ውጭ እርስ በርስ በምርት ሂደት ውስጥ እንዲገናኝ ይገደዳል፡፡ ፍላጎቶቹን ለማርካት ተፈጥሮን እየተቆጣጠረና በምርት ሂደት ውስጥም በሚፈጥረው ግንኙነት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ለሚቀጥለው የእድገት ደረጃ ባያስበው የማቴሪያል ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡ ይህ አዲስ የተፈጠረው የማቴሪያል ሁኔታ እድገና አርጅቶ ከዚያ በኋላ ለአዲስና በህይወ ታዳጊ ለሆነው ህብረተሰብ ቦታውን ይለቃል፡፡ ስለሆነም ማርክስ እንደሚለው፣

" No socialist order ever perishes before all the productive forces for which there is room in it have developed: and new, higher relation of production never appear before the material conditions of their existence have matured in the womb of the old society it self." (2)

አንድ ማህበራዊ ሥርዓት የሚያልፈው፣ በውስጡ ሊዳበሩ የሚችሉት የምርት ሃይሎች ሁሉ ከዳበሩ በኋላ ነው፡፡ በአንድ ሥርዓተ ማህበር ውስጥ፣ ለምርት ሃይሎች መዳበር ሥፍራ እስካለ ድረስ፣ ያ ስርዓተ ማህበር አያልፍም፡፡ እንደዚሁም፣ ከፍተኛ የሆኑ የምርት ግንኙነቶች ህልውና የሚኖራቸው፣ በአሮጌው ሥርዓተ ማህበር ማህፀን ውስጥ ለነርሱ መኖር አስፈላጊ የሆኑት የማቴሪያል ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ነው፡፡ ይህ እስካልሆነ ድረስ፣ አዲስና ከፍተኛ የሆኑ የምርት ግንኙነቶች ሊበቅሉ አይቻሉም፡፡"

እንግዲህ በማርክስ አባባል፣ ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች በፊት፣ አሮጌው ሥርዓት አልፎ አዲስ ሥርዓት ሊመሰረት አይችልም ማለት ነው፡፡

ነገር ግን የካፒታሊስት አልባ እድገት ይህንን የታሪክ ቁስ አካልን ህግ በመሻር አንድ ህብረተሰብ አንደኛውን ዘሎ ወደሌላኛው ይሸጋገራል ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ይህ የካፒታሊስት አልባ የሚባለው 'የእድገት ጎዳና 'አልፎ ተርፎ ለሶሻሊዝም የኢኮኖሚ መሰረት ሊጥል ይችላል ይላል፡፡ R.A. Ulyanovsky የተባለው የሶቭየት ቲዎሬቲሺያን ሶሻሊዝምና አዲስ ነፃ የወጡ አገሮች በሚለው መጽሃፉ ውስጥ እንደሚቀጥለው ያብራራል፡፡

" The god of non-capitalist development is to create the prerequisites for subsequent transition to socialist construction..." (3)

"የካፒታሊስት አልባ እድገት ግብ፣ ለሶሻሊስት ስርዓት ግንባታ አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች/ቅድመ/ መፈጠር /ማሰናዳት/ ነው፡፡"

የታሪካዊ ቁስ አካልነት እንደሚያስተምረውና እንደሚያረጋግጠው ሰዎች ያኛውን ሆነ ይኸኛውን የህብረተሰብ ሥርዓት በመሻት በፈለጋቸው ጊዜና በፈለጋቸው መንገድ አንደኛውን በአንደኛው ለመተካት አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከሱ በቅድሚያ የነበረው ሥርዓት ውስጥ የማቴሪያል ሁኔታዎችን እንደሚፈጠሩም፣ በሌላ ከሱ በፊት በነበረ ወይም ደግሞ ከሱሁለት ደረጃ ወደኋላ ዝቅ ብሎ በሚገኘው ሥርዓት ውስጥ እንዳይደለም ነው፡፡

ይህም ማለት፣ እያንዳንዱ የህብረተሰብ እድገት ደረጃ፣ ለምሳሌ የባሪያው ህብረተሰብ ስርዓት በጣም ወደ ኋላ የቀረ እንደመሆኑ መጠን ከሱ የሚቀጥለውን የእድገት ደረጃ አልፎ ለካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ሊሆኑ የሚችሉ የማቴሪያል ሁኔታዎችን ሊፈጥር አይችልም፡፡ እንዲሁም የፊውዳሉ ኢኮኖሚ ከካፒታሊስት ኢኮኖሚ ጋር ሲወዳደር የምርት ኃይሎች በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙበት በመሆኑ፣ ይህ የህብረተሰብ ሥርዓት ለካፒታሊዝም የሚሆኑ ሁኔታዎችን ባያነቃ የምርት ኃይሎችን በከፍተኛ ቴክኒካዊ መቀየር ላይ መገኘትን ለሚሻው የሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሰረት ሊጥል አይችልም፡፡ የህብረተሰብ እድገት ቅድመ ተከተል አላቸው ማለት ነው፡፡ እንግዲህ እያንዳንዱ የህብረተሰብሥርዓት እድገት ደረጃ አሮጌው ሥርዓት ለአዲሱ ቅድመ ሁኔታዎችን እንዳዘጋጀ ሁሉ ለሶሻሊስት ሥርዓትም የማቴሪያል ሁኔታዎች በበርዥዋው ሥርዓት ውስጥ መፈጠር አለባቸው፡፡ የበርዥዋው መደብ ከሌላ ሥርዓት ውስጥ ከነበሩት የገዥ መደቦች፣ ከባሪያ አሳ

ዓሪና ከባላባቱ የበለጠ ተራማጅ ስለነበር በታሪክ ውስጥ ለምርት ኃይሎች እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። /ይሁንና በርዥዋው ይህንን ያደርገውና የሚያደርገው ከራሱ ጥቅምና አንጻር ቢሆንም በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ይዞታቸው ለሰው ልጅ የወደፊት እድገት መሰረት የጣለ ስለሆነ ማለፍ አይቻልም።/ በመሆኑም ይላል ኤንገልስ፣

"...the productive forces have reached this level of development only in the hands of the bourgeoisie. The bourgeoisie, therefore in this respect also is just as necessary as a precondition of the socialist revolution as the proletariat it self." (4)

የምርት ኃይሎች ይህንን /የካፒታሊስት/ የእድገት ደረጃ የተቀዳጁት፣ በቡርዥዋው አማካይነት ነው። ስለሆነም በዚሁ አንጻር፣ ለሶሻሊስት አብዮት የወዛደሩ መደብ መኖር ቅድመ ሁኔታ የሆነውን ያህል፣ የቡርዥዋም መደብ መኖር የዚያኑ ያህል ቅድመ ሁኔታው ነው።/ ትርጉም የኛ/

ምክንያቱም ሶሻሊዝም ሊመሰረት የሚችለው የምርት ኃይሎች እድገት በከፍተኛ ቴክኒክ ላይ ሲገኝ ስለሆነ፣ ወዛአደሩ በቡርዥዋው መደብ የተፈጠረውን የኢኮኖሚ እድገት ለሰፊና ለሌሎች የተጨቆኑ መደቦች መገልገያ ይውሉ ዘንድ፣ የቡርዥዋውን ሥርዓት አጥፍቶ፣ የሶሻሊስት ስርዓትን በምትኩ በመመስረት፣ ሰው በሰውን የማይበዘበዝበት፣ የምርት መሳሪያዎች በጋራ ንብረት መያዛቸው አስከትሎ፣ ህብረተሰባዊ የሚሆንበትን ሥርዓት ይፈጥራል። ነገ በያዝነው ኢምፔሪያሊዝም ዘመን በሶስተኛው አለም ያሉ የብሄራዊ ከበርቴ መደቦች ልክ እንደተቀደሙ የአውሮፓ የከበርቴ መደብ የታሪክ ተልእኮአቸውን ማሟላት አልቻሉም። አይችሉምም። ይህንንበለአጭሩ ዴሞክራቲክ አብዮት ስናወሳ እንዴት ማሟላት እንደሚችሉ እናያለን።

1.1.1. <u>የካፒታሊስት አልባ እድገትና የማርክስ–ኤንገልስ አባባል፣</u>

የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪ የሚመረኮዘው፣ በአንድ የተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ማርክስና ኤንገልስ ያሉትን በመጥቀስ ነው። ለምን ማርክስና ኤንገልስ እዚህ ግምገማ ላይ ሊደርሱ ቻሉ ? መነሻቸውስ ምን ነበር ?

ማርክስና ኤንገልስ እዚህ ግምገማ ላይ ሊደርሱ የቻሉት፣ TKACHEV የተባለው ራሺያዊ ምሁር ከ 1860 ዓ.ም. በፊት በራሺያ የነበረውን የህብረት እርሻ በማሞገስ፣ ራሺያኖች በልማዳቸው (traditionally) ኮሚኒስት እንደሆኑና ለዚህም የራሺያ ህዝብ ከሰለጠነው ምእራብ አውሮፓ ይልቅ ለሶሻሊዝም የተቃረቡ መሆናቸውን አስመልክቶ የጻፈውን በመቃወም ነው። ማርክስና ኤንገልስ ይህንን የ TKACHOV አባባል ስህተተኛ መሆኑን በማሳየት እንዴት ራሺያ ውስጥ በነበረው ወደ ኋላ ቀር ህብረት እርሻ ምትክ፣ ህብረተሰቡ ባይደርስ ወይም ባይስነጣጠቅ እንዴት ከጥንታዊነቱ ወደ ዘመናዊ ሊሸጋገር እንደሚችል አመለከቱ።

በመጀመሪያ ግን ይህ የጋርዮሽ እርሻ ምን ይመስል ነበር ?

ከ 1861 ዓ.ም. ማለት ጭሰኝነትን የሚያስወግደው ህግ ከመውጣቱ በፊት ገጠር የሚገኘው የራሺያ ገበሬ መሬትን በጋርዮሽ በማረስ ይጠቀም ነበር። ይህ አርቴል /[illegible] በመባል የታወቀው የጋርዮሽ እርሻ አጠቃቀም በተለይም አብዛኛውን ጊዜ በቤተሰብ ገንድ የተሳሰሩ ቤተሰቦች አንድ ላይ በማረስ ይተዳደሩበት የነበረ ነው። ለምሳሌ የአገራችንን የሰሜኑን ክፍል የወሰድን እንደሆነ በተለይም በጎንደር ፣ በትግሬና በኤርትራ በአንዳንድ ቦታዎች በቤተሰብ የተያዙ መሬት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ በማረስ ሲጠቀሙበት ቆይቷል። እንዳ የሚባለው ነው።

ነገር ግን ይህ አርቴል [illegible] በመባል የጋርዮሽ እርሻ አጠቃቀም ጥንታዊ ስለነበር አስተዳደሩ በጣም በዝግታ ነበር። ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች፣ ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ፣ ዘመናዊ አስተዳደር ስላልነበረው ከሌሎች የምእራብ አውሮፓ አገሮች እርሻ አያያዝ ዘዴ ጋር ሲወዳደር ወደ ኋላ ቀር ነበር። ማርክስና ኤንገልስም የአሠን ስርዓት ወደ ኋላ ቀርነት ከተመለከቱ በኋላ፣ በምእራብ አውሮፓ ውስጥ /ማለትም ኢንዱስትሪያላይዝድ አገሮች/ ወዛአደሩ አብዮት አካሄደና ለራሺያ የህብረት እርሻ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ወይንም ዘመናዊ በማዘርጋ ወደፊት ካፒታሊዝም ከሚያመጣው ሰቆቃ ለመዳን ይችላሉ በማለት ተናገሩ።

በመሆኑም ኤንገልስ የሥርአቱን ጥንታዊነት ሲያብራራ እንዲህ በማለት ያቀርባል።

"...it is necessary above all that the artel it self should be capable of development, that it shed its primitive form, in which as we saw it serves the workers less than it does capital, and rise at least to the level of the western European Coorporative."

ከሁሉም በፊት አርቴሉ ማደግ አለበት። እንደተመለከትነው ከሰራተኛው ይልቅ ይበልጥ ካፒታልን ስለሚያገለግል የኋላ ቀርነት ፍጥረቱን አስወግዶ ቢያንስ የምእራብ አውሮፓ የህብረት እርሻእድገት ላይ መድረስ አለበት። /ትርጉም የኛ/

ነገር ግን ይህ የጋርዮሽ ኅብረት ባያድግ ባለበት እንዲቀር ከተገደደ ካፒታሊዝም እየተስፋፋ ሲመጣ ሊስነጣጠቅ እንደሚችል ኤንገልስ አመለከተ። ይሁንና ኤንገልስም በዚያን ጊዜ እንደተመለከተው ካፒታሊዝም በራሺያ በፍጥነት ማደግ ጀምሮ ነበር። በ1861 የተወሰደው ጭሰኝነትን የሚያስወግደው ሪፎርም ገበሬውን ከገባርነት ተላቆ 'ነጻነትን እንዲቀዳጅ' አስቻለው። በተጨማሪም የዛር መንግስት በክሪሚያ /CRIMEAN/ ጦርነት በመሸነፍ ከዚህ ውርደት ለመውጣት ካፒታሊዝምን የሚያስፋፉ እርምጃዎችን ወሰደ። የባቡር ሃዲድ ተስፋፋ። በአንዳንድ ቦታዎች፣ በተፈጥሮ ኢኮኖሚ (natural economy) ፈንታ የገንዘብ ኢኮኖሚ (money-economy) በበፊው ተስፋፋ። በእንጻሩም የጋርዮሽ እርሻ ው /[illegible]/ ተስነጣጥቆ ወደ ገለሰብ ይዞታ ተሸነሸነ። ሆኖም ደግሞ፣ በምእራብ አውሮፓም የተጠበቀው የወዛደሩ አብዮት ሳይደርስ ቀረ። የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ የዚያን ጊዜ ሁኔታ በአጭሩ እንደዚህ ነበር። ዛሬ ግን ይህንን ህቅ ስቶና ወሸንበር በመንዛት፣ በአንድ የተለየ ጊዜና ሁኔታ ማርክስና ኤንገልስ ያቀረቡት ግምገማ በመጠምዘዝ፣ የአብዮት ህግ አድርጎ ለማቅረብ ይሞከራል።

ማርክስና ኤንገልስ በዚያን ጊዜ እንደዚህ አይነቱን ግምገማ ቢያስቀምጡትም ፣ ለአንገዓችም አፍታ ለሶሻሊስት አብዮት መደረግና ለሶሻሊስት ሥርዓት መገንባት የወዛአደሩን መሪነት በፍጹም ወደ ጎን አላተውም። እንዲያውም ደጋግመው እንደገለጹት ካለዚህ መደብ የበላይነት፣ ምንም እንኳ በሌሎች የምእራብ አውሮፓ አገሮች አብዮት ቀድሞ የተካሄደ እንደሆን፣ በራሺያ የወዛደሩ መኖርና መሪነት የመጀመሪያ ቅድመ ሁኔታ /PRE[illegible] መሆኑን አመልክተዋል።

ባጭሩ የማርክስና ኤንገልስ አቀራረብ ለመመልከት እንዲያስችለን፣ 1ኛ አቀራረባቸው ምንአልባታዊ ነበር። 2ኛ ዱሆርባል ህግ አንዓልነበረ 3ኛ የሶሻሊስት አብዮት ይደረጋል ባይሆን፣ ምንአልባት በምእራብ አውሮፓ አብዮት ከተደረገና ወዛደሩ ለአርዓያ

ከመጣ ተንታኞች የህብረት እርሻ ወደ ከፍተኛ የህብረት እርሻ ለማደግ ይችላል፡፡ 4ኛ ሶሻሊስት አብዮት መካሄዱ የግዴታ የወዛአደሩ መናር አስፈላጊ እንደሆነና ከለወዛደሩ መደብ ሶሻሊዝም / መመስረት እንደማይቻል ነው፡፡

1.1.1.1. <u>የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪና የሌኒን አቀራረብ</u>

ማርክስና ኤንገልስ በህይወት በነበሩበት ዘመን ካፒታሊዝም በፍጥነት እያደገ በመሄዱ ላይ ቢሆንም፣ ካፒታሊዝም በቅድመ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም / PRE-MONOPOLY CAPITALISM/ የእድገት ደረጃ ላይ እንዳሉ ሞቱ፡፡ ማለትም በዚያን ጊዜ ከውድድር እየተሸጋገረ ገና በጥቂት ሞኖፖሊስቶች እጅ በመገባትና ከአገር አቀፍ ወደ አለምአቀፋዊነት ለመዛመት ገና መጀመሩ ነበር፡፡ ካፒታልም ሙሉ በሙሉ ዓለም አቀፍ መልክ እየያዘ ስለመጣ፣ የካፒታሊስት ሀገር መንግስትም በሃገር ውስጥ ካፒታል በደከመበት ቦታ ሁሉ እየገቡ የካፒታሊስቶችን ጉን መጠገን የጀመሩትና፣ መንግስታትም የካፒታሊስት መንግስት መባላቸው ቀርቶ ሞኖፖሊ ስቴት ካፒታሊዝም እየተባሉ መጠራት የጀመሩት የመቶ ዓመት ያህል እድሜ ቢኖረው ነው፡፡ ማርክስና ኤንገልስ የካፒታሊዝምን የመጨረሻውን የእድገት ደረጃና በዓለም አቀፍ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ይዘቱ እንደ መጀመሪያው ደረጃ ለመለየት ባይችሉ በመሞታቸው፣ ዛሬም በሶስተኛው ዓለም በመባል በሚታወቁት አገሮች መካሄዱ ስላለበት አብዮት ተቀመው በዝርዝር ለመናገር አልቻሉም፡፡

ይህንን የካፒታሊዝምን አረጃጀና ውስብስብነትና የተመለከተውና በቅድመ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ዘመን በመወለዱና የመጨረሻውን የእድገት ደረጃ ለማየት የቻለው ሌኒን ነው፡፡ በመሆኑም፣ ካፒታሊዝም ያለፈበትን የእድገት ጎዳና በስራው ያጠናውና የኢምፔሪያሊዝምን እድገት በህይወቱ የተመለከተው ሌኒን፣ ይህንን ውስብስብና መዘግዛ ጎዳና፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እድገት ላይ የነበረውን ትርጉም በቅጡ በማጤን፣ በኢኮኖሚ እድገት ወደ ኋላ የቀሩ ሃገሮች ይህንን አስቸጋሪ ጎዳና ሳይጓዙ ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገር እንደሚችሉ አሳየ ለዚሁም ነው ስታሊን፣ ሌኒንን፣ የማርክስና የኤንገልስ ደቀ መዝሙር በመሆን የነሱን ትምህርት በማስፋፋትና የወዛደሩ ትግል ታክቲክና ስትራቴጂ ችግሮች በማዳበር ከአዲሱ ሁኔታ ጋር ያዛመደው ነው ብሎ የጠራው፡፡ በእሱ አነጋገር፣

" Leninism is Marxism of the era of imperialism and the proletarian revolution." (6)

ለምን እነዚህ በኢኮኖሚ ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች በካፒታሊዝም የእድገት ደረጃ ውስጥ ለማለፍ አያስፈልጋቸውም ? ለምንስ አይችሉም ? /በአሁኑ የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ/

ካፒታሊዝም አድጎ ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም በመሸጋገር ላይ እንዳለ፣ እንደቀደሙ በኢኮኖሚ ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች የፍጆታ ሸቀጦችን /CONSUMER .../ ብቻ በመላክ ሊረካ አልቻለም፡፡ የአገሬም ገበያ በገና ለሚያመርተው የኢንዱስትሪ መኪና ሆነ ጥቃቅን ጠበበው፡፡ ማድረግ የነበረበትና አሁንም ሆኖ ያገኘው፣ የፍጆታ ሸቀጦችን ብቻ በአገሬ አምርቶ ከመላክ ይልቅ፣ እዚያው ጥሬ ሃብትና (raw materials) ርካሽ የስራ ጉልበት (cheap labour power) የሚገኝበት ሃገር ምርቱን በአንደኛ ደረጃ ወይንም በሁለተኛ ደረጃ አምርቶ ለገበያ ማቅረብ ሆነ፡፡ እንደቀደሙም ቀላል ምርቶችን ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ካፒታልን ወደ እነዚህ አገሮች እያስገባ የትርፍ ትርፍ ሊያካብት፣ በነዚህ አገሮች ያለው የብሄራዊ ከበርቴው ካፒታሊዝምን በነጻ እንዳያዳብር አፍኖ ያዘው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በመጠኑም ቢሆን የሚያመርተው ብሄራዊ ከበርቴው የሃገሬ ገበያ በውጭ ሸቀጦች ስለተያዘበት፣ ከውጭ ከመጣ ካፒታሊስት ጋር ተወዳድሮ ገበያውን ሊያስለቅቅ አልቻለም፡፡ ከውጭ የሚመጡትም የምርት መሳሪያዎች /የኢንዱስትሪ መኪና/ የካፒታሊስቶችን ትርፍ ማካበቻ ብቻ እንዲሆኑ ታቅደው ስለነበርና የተወሰኑ ስለሆኑ ካፒታሊዝም መልክ ባለው መንገድ እንዲያድግና ተያይዞም

የምርት ኃይሎች በነጻ እንዲያድጉ ማድረግ አልተቻለም፡፡ ጥቂት ከተሞች ብቻ 'ሲለመለሙ' ከ90% በላይ የሚሆነውና በነዚህ ሃገሮች ውስጥ የሚገኘው ህዝብ፣ አሁንም በፊውዳሊዝም የጭቆና ቀንበር እንዲኖር ተገደደ፡፡ /በተጨማሪም ታጠቅ፣ ሚያዝያ 1971 ተመልከት/

ይህንን የተመለከተው ሌኒን እነዚህ አገሮች ወደፊት የሶሻሊስት አብዮት ለማካሄድ ይህንን መዘግዛ መንገድ ባይጓዙና፣ የሶቪየት ወዛደር እርዳታ ካደረገላቸው በሙሉ ባይሆን በአቋራጭ መንገድ መተላለፍ እንደሚችሉ፣ በ1920 ዓ.ም. በሁለተኛው ጉባዔ የኮሚኒስት ኢንተርናሽናል በተነሳው ወደ ኋላ የቀሩ አገሮችን በሚመለከተው የነጥብ ልዩነት ላይ በነዚህ አገሮች ያሉ ኮሚኒስቶች መከተል ያለባቸውን የትግል ስልት አመለከተ፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም የብሄር እንቅስቃሴ (national movement) የቡርዧዎች ዲሞክራቲክ እንቅስቃሴ እንደሆነም አረጋገጠ፡፡ እንዲሁም በነዚህ አገሮች እንቅስቃሴ ቢነሳ፣ አብዛኛው ህዝብ በእርሻ አደርነት የሚተዳደር ስለሆነ፣ ኮሚኒስቶች ከገበሬው ጋር ልዩ ግንኙነት በመፍጠር በትግሉ ውስጥ ለማሳተፍ መቻል እንዳለባቸው አሳሰበ፡፡

ይህ ሌኒን ያስፈረው ቃል ከዛሬ 60 ዓመት በፊት ገና በሶስተኛው ዓለም አገሮች በኢምፔሪያሊስቶች በተከፈተው ኢንዱስትሪ እርሻ አደሩ ወደ ኢንዱስትሪያዎች አምባ እየጎረፈ ወደ ወዛወደርነት በመቀየር ላይ እንዳለና ገና በለጋነቱ ዘመን ነው፡፡ ከ60 ዓመት ወዲህ ገን ሁኔታዎች በብዙ መንገድ ተለውጠዋል፡፡ ይህንን ያህልም የሚጋነን አይሁን እንጂ ኢንዱስትሪያዎች፣ የማመላሻ መንገዶች ባጭሩ ካፒታሊዝምን የሚያስፋፉና አያይዞም እርሻ አደሩ ያርስበት የነበረውን መስክ ትቶ ወደ ከተሞች እየጎረፈ ወዛአደር የሆነው ክፍል የሚናቅ አይደለም፡፡ በትግልም መስክ ቢሆን፣ ለደምዝ ጭማሪ፣ የራሱ ተጠሪ የሆነ የሰራተኛ ማህበር ለማቋቋም፣ ወዘተ... ትግል አድርጓል፡፡ በማድረግም ላይ ይታያል፡፡ ይህም የሚያሳየው የሶስተኛ ዓለም አገሮች የወዛደሩ መደብ ከዛሬ 60 ዓመት በፊት ከነበረው ቁጥርና የንቃት ደረጃ ጋር ሲነፃፀር፣ ዛሬ እየጨመረና የትግል ልምዱም እያገኘ የሄደ አንድ ራሱን የቻለ ኃይል ሆኖ እንደወጣ ነው፡፡ ቢሆንም፣ አሁንም በነዚህ አገሮች አብዛኛው ህዝብ በገበሬና የሚተዳደር ስለሆነ፣ እርሻ አደሩም በፊውዳል የጭቆና የዘረፋ ቀንበር ስለሚሰቃይ የወዛደሩ የትግል አጋር የሚሆን ኃይል ነው፡፡ ስለዚህም በአንዱ በኩል የወዛደሩ መደብ ለብቻው ነፃነቱን ጠብቆ በፖርቲው አማካይነት መደራጀት በሌላ በኩል በወዛደሩና በገበሬው መካከል የሚፈጠር የወዛአደሩና የገበሬው አልያንስ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ይህን ከላይ ያቀረብነው መሰረተ ሃሳብ ከ60 ዓመት በፊት የነበረውንና የዛሬውን ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ልዩነቱን ለማስቀመጥ በማለት ነው፡፡

ይሁንና ሌኒን በሁለተኛው የኮሚኒስት ኢንተርናሽናል ኮንግሬስ ላይ በተነሳው ልዩነት ነጥብ እነዚህ አገሮች እንዴት ወደሶሻሊዝም መጓዝ እንደሚችሉና ከዚያም ቀደመው ምን እርምጃዎች ወይም በምን የእድገት ሂደት ውስጥ ማለፍ እንዳለባቸው በግልጽ አስቀመጠ፡፡ በሱ አባባል፣

"...backward countries can go over to the soviet system and <u>trough certain stages of development</u>, to communism, <u>without having to pass thrcugh capitalist stage</u> ." (7)

" ወደ ኋላ የቀሩ አገሮች በካፒታሊስት የእድገት ደረጃ ውስጥ የግዴታ ባያልፉ፣ ወደ ሶሻሊስት ሥርዓትና በሎም በተወሰኑ የእድገት ደረጃዎች ወደ ኮሚኒዝም ሊሸገሩ ይችላሉ፡፡ /ትርጉም የኛ/

ከዚህ የሌኒን አባባል ሁለት መሰረታዊ ነገሮች መረዳት እንችላለን፡፡ 1ኛ እነዚህ አገሮች ካፒታሊዝም እድገት ወደ ምዕራፍ ካፒታሊዝም እስኪደርስ መጠበቅ አያስፈልጋቸውም፡፡ (without having to pass through) 2ኛ/ ወደ ሶቪየት ሲስተም /ሶሻሊዝም/ ለመሸጋገር በአንዱ የእድገት ደረጃ ውስጥ ማለፍ አለባቸው፡ (through certain stages of development) ነው ይላል ሌኒን፤

" The necessary means for this cannot be indicated in advance" (5) ገጽ 135
" This will be prompted by practical experience" (Ibid)

በመሆኑም እነዚህ ከፊል ፊውዳል ከፊል ካፒታሊስት የሆኑ አገሮች ወደ ሶሻሊዝም ለመሸጋገር እንዲችሉ፤ ከመሸጋገራቸው በፊት ማለፍ ያለባቸው መንገድ ወይም በሌኒን አነጋገር ይህንን ኢንተርሚዲየት (interdidiate) ወይም አደረጃ መንገድ ያለውን የፖለቲካ ሆነ የኢኮኖሚ ችግር መፍታት አለባቸው፡፡ ይህንን ሳያደርጉ በቀጥታ ከፕሪሚቲቭ ኢኮኖሚ ወደ የኢኮኖሚ ስርአት በመሸጋገር የዚያን የኢኮኖሚ ችግሮች በፍጹም ለመፍታት አይችሉም፡፡ ይህም ማለት ይህ ኢንተርሚዲየት መንገድ የራሱ የሆነ የኢኮኖሚ ህጎች እንዳሉትና በዚህም እንደሚገዛ ነው፡፡ ስለሆነም ይላል እንግልስ፤

" Every given economic formation must tackle its own tasks, those which spring from its own bosem and it would be utterly absurd to try tackle the tasks facing another, totaly alien formation" (4)

"ማንኛውም የኢኮኖሚ ስርአት በራሱ ውስጥ የሚፈልቁትን ተግባሮችን ማከናወን አለበት፡፡ ይህንን ሳያደርግ ለራሱ እንግዳ የሆነ ሌላ የኢኮኖሚ ሥርአትን ተግባር አከናውናለሁ ማለት ዘበት ነው፡፡' / ትርጉም የኛ/

ይህም ማለት የፊውዳሉ ኢኮኖሚ ሥርአት በፊውዳሉ፤ የካፒታሊስቱ በካፒታሊስቱ፤ የሶሻሊስቱ በሶሻሊስቱ፤ እያንዳንዱ እራሱን በቻለ የኢኮኖሚ ህግ ይተዳደራል ማለት ነው፡፡

እስካሁን ድረስ ባለፍነው መሰረተ ሃሳቦች በመመርኮዝ የካፒታሊስት አልባ ኢኮኖሚያዊ ሆነ ፖለቲካ ይዘት፤ ምንነትና ትርጉም እናስቀምጣለን፡፡ ይህም የካፒታሊስት አልባ እድገት እንደ እራሱን የቻለ ሥርአት ነው፤ ወይንስ አይደለም የሚለው መደምደሚያ ላይ ያደርሰናል፡፡

1.2. የካፒታሊስት አልባ እድገት የኢኮኖሚ ይዘት፡፡

ከላይ እንዳስቀመጥነውና እንገልስም እንደሚያስቀምጠው፤ ማንኛውም የህብረተሰብ ሥርአት የራሱ የኢኮኖሚ ችግሮች መፍታት እንዳለበት፤ የራሱም ሆነ ልዩ የኢኮኖሚ ህግ (specific law)እንዳለውና ይህንን ሳያደርግ ለሚቀጥለው የኢኮኖሚ ሥርአት የማቴሪያል ሁኔታዎች ማገዝና እንደማይችል ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የሌኒን፤ ከሱ በፊት የሚገኘን፤ በኢኮኖሚያዊ ሆነ በፖለቲካ ይዘቱ ለሱ እንግዳ የሆነን የኢኮኖሚ ስርአት ችግር መፍታት በፍጹም እንደማይችል ነው፡፡

የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪስ ምን ይላል ?

ይህ ቲዎሪ እንደሚለውና 'ሊያስቀምጡ 'እንደሚሞክሩት፤ በቅድመ ካፒታሊስት pre-capitalist የእድገት ደረጃ ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች የካፒታሊዝምን የእድገት ደረጃ በፍጹም ሳይነኩ ሶሻሊዝም ሊገነቡ ይችላሉ ይላል፡፡ ስለዚህም ሥልጣኑን የጨበጠው መደብ

/የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ መሰረት ይህ መደብ የከፍተኛው ንኡስ ከበርቴ ወይም የንኡስ ከበርቴው መደብ ነው/ ፀረ-ፊውዳል፤ ፀረ-ካፒታሊስት፤ ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ኢኮኖሚ መስመር በመከተል ለሶሻሊዝም መሰረት ለመጣል ይችላል ይለናል፡፡

በመሆኑም ይላል ይህ ቲዎሪ፤

" The non-capitalist way is, above all, the way towards creating the material prerequisites for the building of a socialist society. Non-capitalist development is a transitional historical stage, a stage of anti-imperialist, anti-capitalist and anti-feudal transformations." (10) / ትርጉም የኛ/

'የካፒታሊስት አልባ እድገት ከሁሉም በፊት የሶሻሊስትን ሥርአት ለመገንባት የሚያስችሉትን የማቴሪያል ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያገለግል መንገድ ነው. የካፒታሊስት አልባ እድገት ለሽግግር የሚሆን የታሪክ ደረጃ /ወቅት/ ነው የፀረ-ኢምፔሪያሊስት፤ ፀረ-ካፒታሊስትና የፀረ-ፊውዳል ሽግግር ነው፡፡' /ትርጉም የኛ/

የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪ ከዚህ በላይ የጠቀስነውን ካሰፈረ በኋላ፤ የመሸጋገሪያው ወቅት በምን ኢኮኖሚ ህግና ሥርአት እንደሚገዛና እንደሚተዳደር አይገልጽም፡፡ እንዴ፤ ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሰረት ሊጥል የሚችል ሥርአት ከሆነ ደግሞ እንዴት ሙሉ በሙሉ 'ፀረ-ካፒታሊስት' በመሆን ከሱ ጋን እየተያረኑ ሊያድጉ የሚችሉትን የምርት ኃይሎች ሳያበድግ ለሶሻሊስት ሥርአት መሰረት ሊጥል ይችላል ? በሶሻሊስት የኢኮኖሚ ህግ እንዳይለን ፖለቲካዊ /የመዝ አደሩ መደብ እጅ ሥልጣን ሳይገባ/ ሆነ የማቴሪያላዊ ሁኔታዎች አይፈቅዱም፡፡ አይቻልም በካፒታሊስት የኢኮኖሚ ህግ እንዳይለን ደግሞ ካፒታሊዝም እንዳያድግ በገነብ አጠሩት/አፍኑት/ ይላል፡፡ ስለዚህም በሱ አባባል የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ህግ አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ብለን እንዳስቀመጥነው፤ ህብረተሰብ ባለፈባቸው የእድገት ሂደት ውስጥ ከወርድ ጋር የሽ እስከ ባሪያ፤ እያንዳንዱ የራሱ የኢኮኖሚ ህጎች እንደነበሩትና በነሱም እንደተዳደረና እንደሚገዛ የአንደኛው በአንደኛው እንደማይገዛ ማርክሲዝም ያስተምረናል፡፡ ነገር ግን ይህ ማለት በሁለት የተለያዩ ስልተ ምርት ጎን ለጎን የሚሄዱ ለምሳሌ ገማሽ ፊውዳልና ገማሽ ካፒታሊስት በነበሩና አሁንም ባሉ አገሮች የፊውዳሉም ሆነ የካፒታሊስቱም የኢኮኖሚ ህግ አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን በካፒታሊስት ህብረተሰብ ለሶሻሊዝም የሚሆኑ መሰረቶች /የማቴሪያል ሁኔታዎች ይኸውም እንደ የምርት ኃይሎች በከፍተኛ ቴክኒክ ላይ መገኘት/ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ህግ ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሶሻሊስት ሥርአት ሰው ሰውን የሚበዘብዝበት ሥርአት አጥፍቶ የምርት መሳሪያዎችን ከግላዊነት ወደ ማህበራዊነት የሚያሸጋግርና የህብረተሰቡም የማቴሪያልና የባህል ፍላጎት እንዲሟላና ምርቱ እየበረና ከብዛት ወደ ጥራት እያደገ እንዲሄድ በከፍተኛ ቴክኒክ ላይ ተመርኩዞ የሚጓዝ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም ከሌሎች የኢኮኖሚ ህጎችጋር ጎን ለጎን ተቀምጦ የማይኖርና አብሮ በማይጓዝ ህግ ይገዛል፡፡ እዚህ ላይ ሶሻሊዝም ከሌሎች የኢኮኖሚ ህጎች ጋር ሲል ከዋናው በቻ እንጂ፤ በሶሻሊዝም፤ የካፒታሊዝም አንዳንዱ ህጎች ውስን ሚና አላቸው ግን ዋናው ህግ ይህ አይደለም፡፡ ለምሳሌ law of value --- መጠነኛ ወይም ውስን ሚና አለው፡፡ የፊውዳሊዝምና የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ አውታሮችና ህጎች በእድገት ደረጃና /በአይነቱ/ በቅርጽ ይለያዩ እንጂ ሁለቱም የበዘበዛ ሥርአት አውታሮች እንደመሆናቸው መጠን ለአንዱ ለተወሰነ የታሪክ ወቅት ተቻችለው ጎን ለጎን ሊሄዱ ይችላሉ፡፡ ይሁንና በየራሳቸው የኢኮኖሚ ህጎች እየተዳደሩ በቻ እንጂ አንደኛው አንደኛውን በመቆጣጠር አይደለም፡፡

ይህንን ከተመለከትን በኋላ፣ የካፒታሊስት አልባ እድገት የሚያዝበት የኢኮኖሚ ህግ በካፒታሊስት አልባ ነው ቢባል እንኳ በህብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ ያልነበረና የማይ ኖር፤ የህብረተሰቡም እድገት እንደሚያሳየው በዚህ 'ስረአት'ውስጥ ያልታለፈና የማይታለፍ በመሆኑ እራሱን የቻለ የኢኮኖሚ ሥርአት እንዲሁም የሚተዳደርበት ልዩ የኢኮኖሚ ህግ አይኖረውም ማለት ነው። እራሱን የቻለ የኢኮኖሚ ሥርአትና ህግ የሌለው የእድገት ጎዳና ደግሞ በምን ተአምር ለሚ ለሚተተለው ሥርአት የማቴሪያል ሁኔታዎችን ሊፈጥር ይችላል ?

ለነዚህ ጥያቄዎች መልሱ የለም። የዚህ ቲዎሪ ፈጣሪዎች ለካፒታሊስት አልባ እድገት ጎዳና 'በተግባር መመንዘር' እንደ ዋና ተቀዳሚ ሁኔታ (preconditions) አድርገው የሚወስዱት ባጭሩ የሶሻሊስት አገሮችን መኖር ነው። በመሆኑም ይላሉ

" The idea that the non-capitalist way of development <u>only become possible</u> thanks to the suport of socialist community..." (11)

'የካፒታሊስት አልባ እድገት በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው፣ ለሶሻሊስት ኮሚኒቲ መኖር ምስጋና ይግባቸውና በእነሱ እርዳታ ብቻ ነው፣'

በእርግጥ 'ሶሻሊስት ኮሚኒቲ' የተባለው፣ የማቴሪያል ሁኔታዎች ከፈተኛለት፣ ለ ነጻነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለሶሻሊዝም የሚታገሉ ኃይሎችን ባለው አቅምና ችሎታ መርዳት ብቻ ባይሆን ግ[illegible] አለበት። ይህ ማለት ግን አንዱ የሶሻሊስት ሃገር በሆርን አይደለም በዚያ አገር ውዝ-አደርፈዋር፣ አደራጅቶ፣ የኮሚኒስት ፓርቲ መስርቶ፣ አብዮት በዚህን ጊዜ ታካሂዳለህ ብሎ ይህንን ወይንም ያኛውን የኢኮኖሚ ህግ ተጠቀም ብሎ ሊረዳው አይችልም። በአብዮት ህግም አለመቻል ብቻ ባይሆን አይፈቀድም።

የካፒታሊስት አልባ እድገት ጎዳና የራሱ የኢኮኖሚ ህግ የሌለው ብቻ ባይሆን፣ ቲዎሪው ራሱ በቅራኔዎች የተሞላ ነው። በሚያወባው ቲዎሪም ውስጥ መሬት ከባላባቶች ተነጥቆ ለደሃ ገበሬዎች መሰጠት እንዳለበት ይናገራል። ይህ ማለት ምን ማለት ነው ? ከዚህ በፊት በጥቂት ገለሰቦች እጅ የነበረ ወደ ደሃ ገበሬ ዎች ተዘዋውሮ እነሱ በግረስ ለራሳቸው ይጠቀሙበ ታል ማለት ነው። እንዳይሸጡ እንዳይለውጡ ቢደረግም የምርት መሳሪያዎችና /ማጭዱ፣ ምፈር፣ ቀንበር፣ በሬው ወዘተ./ ያረሱት ምርትም ውጤት የራሳቸው የግል ነው። ካረሱት ምርት የተረ ፋቸውን ገበያ አውጥተው ሸጠው ለራሳቸው የሚሆን የፍጆት እቃዎችንም ሆነ የምርት መሳሪያዎችንም ገዝተው ይጠቀሙባቸዋል። በዚህም በሰሬው የእቃ ልውውጥ ይስፋፋል። ይህም ማለት ባጭሩ ካ ፒታሊዝም ማስፋፋት ማለት ነው። ነገር ግን ይህ የካፒታሊስት አልባ እድገት በእንዲበኩል ካ ፒታሊዝም እንዳያድግ፣ በገነበ አጠራት በሌላ በኩል ደግሞ ካፒታሊዝምን የሚያስፋፋውን መሬት ከጥቂት ባላባቶች ነጥቆ ለደሃ ገበሬዎች መሰጠት አለበት አያለ እርስ በራሳቸው የሚጋ ሃሳቦች ያቀርባል።

1.3 <u>የካፒታሊስት አልባ የፖለቲካ ይዘት</u>

የካፒታሊስት አልባ እድገት ለማሳመን እንደሞከረው፣ የወዝ አደሩ መደብ ባይሆን፣ የንዑስ ከበርቴው መደብ፣ በዚህ ፈለግ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን አየመራ/ወዝአደሩንም ጭምር/ የዲሞክራቲክ አብዮትን አካሂዶ ሶሻሊዝምን ለመመስረት ይችላል። በዚህ ቲዎሪ መሰረትም፣ የወዝአደሩ ቀጥር በሶስተኛው ዓለም አገሮች አነስተኛ ስለሆነ ወይንም ደግሞ ስለማይኖር የዲሞክራ ቲክ አብዮትን ሊመራ አይችልም ማለት ነው። በመሆኑም ይላል ይህ ቲዎሪ፣

"...it is the petty-bourgeois intelligentia which comes to constitute the dominant political force." (12)

ይህ ማለት ምን ማለት ነው ? ገኛ/ የንዑስ ከበርቴው መደብ በአጠቃላዩ ቢ ታይ ፍጹም አብዮታዊ ሃይልና፣ ሌሎች የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን አየመራ

የዲሞክራቲክ አብዮትን ከፍጻሜ ያደርሳል ማለት ነው። ይህንን ካደረገ ደግሞ ሶሻሊዝምን ግን [illegible] መደብ የለሽ ህብረተሰብ /[illegible]/ ይሸጋገራል ማለት ነው። የዚፈን ዓር ዓይ [illegible] ነው እንጂ የቲዎሪው ጥና የዚችና አንዝጋቢነት ምልዓን በዚህ ወሳኝ በሆነው መ[illegible] እንዲገባ የተደረገና የሚደረገ ጥረት ነው። ምክንያቱ ቀላል ነው። ንዑስ ከበርቴው በ[illegible] ኃይል ስላልሆነ እንዱ የሚወጋውን ኃይል መፈለግ እና የርም ከሚለው አስተሳሰብ የ[illegible] ነው። 2ኛ/ የወዝ አደሩ መደብ በዚህ አብዮት ውስጥ /በካ.አ. መሰረት [illegible] የለም [illegible] ቦታ ሊኖር አይችልም/ ቢኖር እንኳ ተከታይ እንጂ መሪነትን ይከዳል። ስለ ሆነ ይህ የካፒታሊስት አልባ እድገት ጎዳና እንደሚከተለው አድርጎ ይተርትልናል።

" The non-capitalist path of development could be interpreted... when the bloc of anti-imperialist, progressive social forces that from a numerical point of view is dominated by non-proletarian working masses, represented in political affairs first and foremost by intermediate strata, the petty-bourgeois. intelligentia,... using non-capitalist methods thus laying the foundation for the subsequent transition to a socialist path." (1[illegible])

ከላይ እንደሰፈረው፣ ይህ የካፒታሊስት አልባ እድገት ፀረ-ኢምፔሪያሊስት የሆኑ ሀይሎችን ያቀፈና ወዝ አደር ያልሆነውን በፊ በሬተኛ በቁጥር የበላይነት ያለው፣ በፖለቲካው ፊገሮ ንዑስ ከበርቴው እንደሚመራውና በዚህም መደብ ለሶሻሊዝም መሰረት መጣል እንደሚችል ነው።

በሌላ ወገን ከላይ ያስቀመጥነውን ሃሳብ በመቨር / በይዘት ግን ያው ነው / የተጠቀሱትን ሃይሎች በአጠቃላይ ባይሆን ከረዥምና ከተወሳሰበ ትግል በኋላ የሚወጡት የመጠረቨያዎች የብሄራዊ ዲሞክራቲክ አረማጆች የሆኑት ለሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሰረት ሊጥሉ ይችሉ ይሆናል ይላል ሀሳቡም እንደሚለው፣

" As result of gradual and protracted changes the finest representatives of national democraty <u>may</u>, apparently, make the transition to the principles of scientific socialism." (Ibid)

በእርግጥ በሁለቱ አቀራረቦች መካከል እርስበርሳቸው አለመጣጣም ቢኖርም፣ አሁንም በሆነ ምልዓኑን የመጠረቨ መጠረቨ አያደላደለ የሚወጣው ይቨው የንዑስ ከበርቴው መደብ ነው። የካፒታሊስት አልባ ለማሳየት እንደሞከረው፣ በነዚህ ኃይሎች መካከል የሚኖረው ትግል የሁለት መስመር ትግል ባይሆን ወይንም ደግሞ ለሶሻሊዝም በሚታገሉና አሁን በሚታወቁ ባይሆን፣ ለሥልጣን የበላይነት በሚታገሉ/በሚሹ/ ኃይሎች መካከል ነው ማለት ነው።

ከላይ ባስቀመጥነው መልክ፣ በየመስመሩና በየገጹ በዙ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ወይንም ዥጉ ነገሮችን አየጠቃቀስን ባለፍን ነበር። ሆኖም ግን አሁን ከማርዝም ጋር መስ ረታዊ ነገሮች አይደሉም። ሌላም እንደዚህ ባደረገን ቁጥር አሁኑ በጥቅስ ይሞላና እንገበያን ያሰለቻል። ስለዚህም ወደ ዋና ፍሬ ነገሮች ላይ ብናተኩር የተሻለ ይመስለናል።

ማርክሲዝም እንደሚያስተምረን ከማንኛውም መደቦች ይልቅ የንኡስ ከበርቴው መደብ የሚዋዥቅና ወላዋይ ነው። በተለይም ወደ ላይ ወደ ላይ ለመንጠራራት ካለው ፍላጎት / የከበርቴ ቦታ ለመውሰድ/ የተነቢ ከበታች ያሉትን መደቦች ለጊዜው እንዲያገዙት በፈለገም፣ ፍላጎቱ

ከተሳሉ በኋላ እንደገና ከአድሃሪ ኃይሎች ጋር ተባብረው የቆዩ አጋሮቹን እንደሚያገ በታሪክ የታየ ነው፡፡ በእርግጥ ከዚህ መደብ የወጡ ጥቂት አብዮታዊ ምሁራን ከወዝ አደሩ ጋር በመቆየት የወዝአደሩን ምሬትና የአኗኗር ዘዴ አኗኗራቸው አድርገው በመውሰድ በኀንበር ቀደምትነት አብረውት ይበለፋሉ፡፡ ገን እነሱ በቻቸውን ተነጥለው ኀንበር ቀደም ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ንዑስ ከበርቴው እንዳለ ገን እንደወዝአደሩ መደብ አብዮታዊ ሚናን ሊጫወት አይችልም፡፡ የራሱን ጥቅም ትቶ ለሌላ መደብ ጥቅም እንዳሉ ሊታገል ይችላል ማለት / ስለዚህ መደብ ብቻ ሳይሆን ለዩ ለዩ መደቦችን በንመለከት / እንደም ስለዚህ መደብ ውስንነት አለመረዳት ነው፤ ወይንም ደግሞ የወዝአደሩ አጋዥ መስሎ ወዝአደሩን ለመዋጋት የሚደረግ ደባ ነው፡፡ ምክንያቱም ሌኒን እንደሚለው፤ "No class fight against himself" እንዲሁም ከአብዮት ታሪክ እንደምንማረው የንዑስ ከበርቴው መደብ በቻውን የቆመ ኃይል እንዳልሆነ እንዲያውም በተወሰነ አብዮታዊ ወቅት የመደብ ትግል ሲፋፋም ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በመወላወል ጠባዩ እየተገመ ወደወዝአደሩና ሌሎች የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ባይሆን የሚጠጋው፤ ወደ ፀረ-አብዮት ኃይል እንደሚያደላ እንጂ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ እንደሚለን ሶሻሊስት አብዮትን በቆራጥነት እየመራ መውሰድ ያለባቸውን ፖለቲካዊ ሆነ ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች በተግባር እየመነዘረ ወደፊት የሚጓዝ አይደለም፡፡ በዚህም አብዮታዊ ወኔ በሌለው መደብ የሚመራ ሶሻሊዝም ደግሞ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርእዮተ አለም የታነጸ የወዝአደሩ የሚገነባው እውነተኛው ሶሻሊዝም ሳይሆን፤ የንዑስ ከበርቴው ሶሻሊዝም የሆነ ሌላ ዓይነት የብዝበዛ ስርአት የሚመሰረትበት ነው ማለት ነው፡፡

ይህን በአብዮት ታሪክ ውስጥ የታየን የንዑስ ከበርቴውን የመዋዠቅ ጠባይና የፀረ-አብዮት ሚና ወደ ጎን በመተው የመደቦችን ትግል የምሬትና የታማኝነት ጉዳይ አድርጎት ቀጥ ይላል፡፡ ስለሆነም ይላል ይህ ቲዎሪ በሚያሳዩት ትልቅ ታማኝነት፤ ለአብዮታዊ ለውጥ ያላቸው ምኞትና ወደበራተኛው ህዝብ ሊያስጠጋቸው፤ የቡርዧዎን ቲንዴንሲና የቡርዧዎን ሪፎርሚዝም አይፈልጉም በሉ አስቲኝ የሆነ ነገር ያስፍራል፡፡ በቲያሪውም አባባል፤

" The greaterloyality to revolutionary ideals shown by this circles (petty-bourgeois)...the more intolerant they will be of bourgeois tendencies and bourgeois reformism,...he in the vanguard of the people...to the preparation of the necessary conditions for the construction of socialism in economically backward countries." (15)

ይሄ ሠንጣ ኖሮ ለምን አብዮት አዳካሚ ነው፤ መዝግዛ ነውተባለ ? በተለይም በገጠር ካፒታሊስት በገጠር ፊውዳል ህብረተሰብ ውስጥ በቁጥር የተማረው የንዑስ ከበርቴ መደብ ይበልጣል፡፡ ካልተማረውም ሠገ በቁጥር አይሉ የሚገኘው የንዑስ ከበርቴው መደብ ነው፡፡ / አርሶ አደሩም ይጨምራል/ ይህ መደብ ከራሱ ጥቅም ባሻገር በመለከት ኖሮ ባለው ችሎታና እውቀት እራሱንና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን አደራጅቶ ወደ ነጻነት በመራቸው ነበር፡፡ ከነሱ ጋር ተባብሮ የበለጸገና የነጻነት መሰናክል የሆኑ የፀረ-አብዮት ኃይሎችን ጠራርጎ በጣላቸው ነበር፡፡ እንደዚህም ባለመሆኑነው፤ ከጉልበቱ በስተቀር ሌላ የሚሸጠው ነገር የሌለውና ከተፈጠረ አንስቶ ትንሽም ሠገ ከካፒታል ጋር እየተፋጠጠ ያለው መደብ ወዝ አደሩ ብቻነው፡፡ማርክስም እንዳለው፤ የወዝአደሩ መደብ ከተተበተበበት የጭቆና ሰንሰለት ሰብሮ ከመውጣት በቀር የሚያጣው ነገር የለም፡፡ በመሆኑም እራሱንና ሌሎችን የህብረተሰብ ክፍሎች ነጻ የሚያወጣው መደብ እራሱ ብቻ ነው፡፡

1.3.1. የካፒታሊስት አልባ - እድገት መንግስት ምን ይመስላል ?

የካፒታሊስት - አልባ መንግስት፤ በወዛደሩ የሚመራ፤ በወዝአደሩ አርሶ አደሩ እንዲሁም እንዲሁም ሌሎች ፀረ- ባላባታዊ ፀረ- ቢሮክራሲ ካፒታሊስት [illegible] መንግስት ሳይሆን፤ የሚመሰረተው፤ ንዑስ ከበርቴውን ወዝ አደር ያልሆነውን ገጠር ወዝአደር እንዲሁም ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን በማቀፍ ነው ይላል፡፡ በዚህ ቲዎሪ መሰረት የብሄራዊ ዴሞክራቲክ መንግስት የሚቀጥለውን ይመስላል፡፡

"...a national democracy is defined as a revolutionary dictatorship /the petty-bourgepis dictatorship [illegible] /of semy proletarian working masses and petty bourgeois strata of all anxious..." (16)

ይህ ንዑስ ከበርቴውን ወዝአደር ያልሆነውን ገጠር ወዝ አደር የሆነውን ያቀፈ መንግስት በምን ተአምር የሌሎች የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም ያስጠብቃል፡፡ እንዲያው ለማወናበድ ካልሆነ በስተቀር ገጠር ወዝአደር ማነውን ከፍል እስከአሁን በታየው በአንዳንድ ሀገሮች 'የእድገት ጎዳና 'ያራምዳሉ በሚባሉ አገሮች ፍጹም ተግባራዊ የለውም፡፡ ይሁንና መንግስት ደግሞ በምንም አይነት የሁሉን መደቦች ጥቅም በእኩል ሊያስጠብቅ አይችልም፡፡ በመደብ በተከፋፈለ ህብረተሰብ ውስጥ እስከአሁን በታሪክ እንደታየው መንግስት የሁሉን መደቦች ጥቅም የሚያስጠብቅ ሳይሆን፤ በመደቦች መካከል ካለው ግጭት ውስጥ የተፈጠረ ',ሳአሳይ መቆር ነው፡፡ ነገር ገን የወዝአደሩ መደብ እንደ ከሌሎች መደቦች ጋር ሲወዳደር አብዮታዊ ስለሆነ፤ ሁለተኛ ሶሻሊዝምን መስርቶ ወደ መደብ የለሹ ህብረተሰብ ለመሸጋገር / ለማምራት/ ስለሚፈልግ፤ ከዚህ በፊት ሌሎች የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የራሱ አጋር በማድረግ የእነሱንም ጥቅም በመጠበቅ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ይገነባል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ወዝ አደሩ ይህንን የሚያደርገውም ህብረተሰቡን በራሱ አምሳል ለመለወጥ ካለውም ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡ የሱ ፍላጎት ሌላ ሳይሆን ወዝአደራዊ ባህል የሰፈነበት፤ ብዝበዛ የሌለበት፤ ወዘተ. ሥርአትን መገንባት ነው፡፡

ይህ የካፒታሊስት አልባ እድገት ለማሳየት / ለማሳመን/እንደሚፈልገው እንደሚ ምክሮና ምሳሌ የሚወስደው፤ ይህንን የእድገት ጎዳና የሚያራምዱ መንግስታት ነበሩ፤ ለምሳሌ፤ በርማ፤ ኢራቅ፤ ሱሪያ፤ ደቡብ የመን፤ አልጄሪያ የወዝአደሩንና የሌሎች የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም እንደሚያስጠብቁ አድርጎ ነው፡፡ በነዚህ አገሮች ያሉት የሲቪልም ሆነ የወታደር / አብዛኛውን ጊዜ ወታደር / መንግስታት የካፒታሊስት አልባ እንደሚያወራው ዴሞክራቶች ሳይሆኑ በፀረ-ዴሞክራሲነታቸው የታወቁ ናቸው፡፡ ወዝ አደሩ እንኳ በነጻ ሊደራጅ የማይችልበት ሃገሮች ናቸው፡፡ በስልጣን ያሉትም የከፍተኛው ንዑስ ከበርቴ መደብ የሆኑና የሚያራምዱትም የመንግስት ካፒታሊዝምን / አድሃሪ የሆነውን / የሚባለውን በቢሮ ከበርቴያች፤ በደራሽ ከበርቴዎች የሚተዳደርን ኢኮኖሚ ነው፡፡ ይህ ማለት ምን ማለት ነው ? 1ኛ/ የተወረሱት የኢንዱስትሪ መኪናዎች በሙሉ ማህበራዊ አይደሉም፤ 2ኛ/ በየኢንዱስትሪዎቹ የተሾሙት ዳይሬክተሮች በቀጥታ የመንግስት ሥራ አስፈጻሚዎች ናቸው፡፡ በጥቅም የተሳሰሯ በመሆናቸው ከኢንዱስትሪዎች ምርት [illegible] የሚገኘው ትርፍ፤ በአንድ ወገን እነዚህን ሥራ አስፈጻሚዎች ቢሮክራቶች እንዲሁም በየመንግስት መሥሪያ ቤት የተሾሙትን ቢሮክራቶችና እራሱን በስልጣን ላይ ያለውን መደብ ማደለቢያ ሲውሉ፤ በሌላ ወገን ደግሞ የገዢው መደብ ለፖሊስና ለወታደሩ የመጠቀሚያ መሳሪያዎች ማጠናከሪያ የሚጠቀምበት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ በጠየቶች 'ተራማጅ ነው 'በሰው የሚጠራ መንግስት ካፒታሊዝም (progressive state capitalism) ፤ ለወዝአደሩ ኑሮ ማሻሻያ፤ ለምርት ኃይሎች ማሳደጊያ የሚውል አይደለም፡፡ በምርት ሂደት ውስጥም የወዝአደሩ

መደብ የራሱን ተጠሪ በመምረጥ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ተሳትፎ የለውም። ስለሆነም በነዚህ አገሮች ያለው ተራማጅ የመንግስታት ካፒታሊዝም ባይሆን አዉሃሪ የሆነ፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርአት ላይ ያልተገነባ፣ የምርት ኃይሎችን እድገት የሚያፋን አየርጂያዊ ስርአት ነው ማለት ነው።

1.3.1.1. የካፒታሊስት አልባ እድገት በዲሞክራሲ ላይ ያለው አመለካከት፣

የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ የእነዚህን አገር መንግስታት እንደተራማጅ አድርጎ ማቅረቡ ብቻ ባይሆን በዲሞክራሱ ተግቶ ላይ ያለው አስተያየት ፍጹም አዉሃሪና አሳይንባዊ ነው። ስለዲሞክራሲ ቢያወባም፣ ከመሬት መወረስ፣ ከማምረቻ ከባንኮች ወዘተ. ናሽናላይዜሽን መሆን ጋር ጥምርም የዲሞክራሲ መብቶች ተግቶ መሬታት፣ እንዲሁም የእነዚህን / የተወረሱትን / በቀጥታ ወደ ሰሬው እጅ የሚገቡትና ለሰፊው ህዝብ ጥቅም የሚውሉት ከዲሞክራሲ መብቶች መለቀቅ ጋር መያያዙን በፍጹም አያመለክትም። በመሃከላቸው ያለውን ዲያለክቲካዊ ግንኙነትም በፍጹም አይረዳም፣ ይሁንናም፣ በቲዎሪ መሰረት የካ.አልባ እድገት ጎዳናን የሚከተሉ ሃገሮች በፍጹም የቡርዧዋውን ዲሞክራሲ አንቀበልም በለዋል ይላል። ነገ ደግሞ በዚሁ ቲዎሪ በቻ ወይንም የእድገት ጎዳና የሚናረውን ዴሞክራሲ ባይነገረን ይቀርና፣

"...as is the case of the majority of the third world countries, the institutions of political democraty are not being developed to the necessary degree." (16)

ምክንያቱም ይላል ይህ ቲዎሪ በመቀጠል፣

" The objective prerequisites for this are lacking namlly, a specific cultural, social and economic level and traditions of political life." (Ibid)

እንደዚሁ ዓይነቱ አባባል የቡርዧዋው አፖሎጂስቶች ይሉታል።

በኛ ግምት ግብዝነት ነው። በነዚህ አገሮች ላለው ቀርቶ ትንሽ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ወይንም የቡርዧዋ ዲሞክራሲ እንኳን ቢኖር ኖሮ፣ የካፒታሊስት አልባ እድገት እንደሚለን ባይሆን፣ በተቃራኒው ከአርጌው አስተሳሰብ / ኮምልክ / እየተላቀቁ ይበልጡኑ በባህል በ በሻል በፖለቲካ እንዲሁም በኢኮኖሚ በተራመዱ ነበር። ሆኖም ግን በነዚህ አገሮች የዲሞክራሲ መብቶች በመታፈናቸው፣ በያቸ ህብባቸውን ሊያገኟፈራሽሩ አልቻሉም። አይችሉም። አዳዲስ ህብበችዓ በማፍለቅ ለእድገት የሚሆናቸውን መንገድ መቀየስ አልቻሉም። የባህልን የበሻሉን የፖለቲካን /እድገት/ መሻሻል ከዲሞክራሲ መብቶች ነጥሎ መመልከት፣ የዲሞክራሲ መብቶች በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ መኖር ያለውን ወሳኝ ሚና አለመረዳት ነው። ወይንም ደግሞ ውዥንበር መንዛት ነው። ስለዚህም አንድ መንግስት የበለጠውን ዲሞክራቲክ በሆነ ጥግር ወዘአደሩ ገበሬው እንዲሁም ሌሎች የተጠቁ መደቦች በትግላቸው በተቀዳጁት የዲሞክራሲ መብቶች ትግላቸውን እያስተባበሩና እያስተባበሩ፣ ከጥገኛ አስተሳሰብ እየተላቀቁ አዲስና ለትግላቸው የሚሆኑ አመቺ ሁኔታዎችን እየፈጠሩ ወደፊት ይራመዳሉ። እንደዚሁ ነው እንጂ መመልከት የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ እንደሚለን በመጀመሪያ ቋሪያ በሬ ከዚያ በኋላ ገደግ አይደለም።

1.3.1.1.1. የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪና የላእላይ መዋቅር ጉዳይ፣

የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ፣ ይህ ነ የእድገት ጎዳና በሚከተሉ ሃገሮች ያለውን ላእላይ መዋቅር / super structure / አስተኛ በሆነ መልክ ያስቀምጣል።

እንደሚለነው፣

" These (stated above) contradictions between progress and backwardness, between a socialist perspective and concrete economic and cultural levels determine to a considerable extent the development of the state political super structure in the countries which are embarking on the non-capitalist path." (17)

ነገር ግን ዲያለክቲካዊ ቁስ አካል እንደሚያስተምረን፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለው ቅንጅት የኢኮኖሚውን ሥርአት ቤሬ ዋር ላእላዩ መዋቅሩም የሱ ነፀብራቅ ነው። ማርክስም እንደሚለው፣

" The sum total of this relations (production relation + productive forces) of production constitutes the economic structure of the society, the real foundation on which rises a legal and political super structure and to which correspond definite forms of social consciousnes." (18)

ከላይ ማርክስ እንደሚለው የኢኮኖሚው ሥርአት ላእላይ መዋቅሩን በዋነኝነት ሲወስን፣ ላእላይ መዋቅሩ ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ወይም የሚኖረውን የባህል፣ [illegible] ወዘተ . ጎታ ደረጃ ወይንም የአስተሳሰብ ሁኔታ ያንፀባርቃል።

የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ ግን ከላይ ያስቀመጥነውን ባይገባ ሃቅ በመቃረር ወራ-ማርክሲስት ገምገማ ብቻ ባይሆን አደገኛና የተሳሳተ ውዥንበር ይነዛል። በለላ በኩል ም ገና ባልተፈጠረ፣ በለላ፣ ነገር ግን ወደፊት በሚመጣው የሶሻሊስት ፔሪስፔክቲቭና አሁን ያለው የኢኮኖሚና የባህል እድገት ደረጃ በምን ተከምር ቅራኔዎች እንዳሉ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። የመጀመሪያው ማለት 'የሶሻሊስት ፔሪስፔክቲቭ' ገና በጥንቃቄ ውስጥ የሚገኝ ነው። የኃለኛው ግን የኢኮኖሚና የባህል እድገት ደረጃ ያለ ስለሆነ፣ በነዚሁ የካፒታሊስት አልባን እድገት በሚከተሉ አገሮች ቅራኔው / መሰረታዊ/ በነዚሁም በኩል ሊሆን አይችልም። ይህም ባለመሆኑ በነዚህ አገሮች አንድ ላይ በመደመር የፖለቲካ ላእላይ መዋቅሩን አይወስኑም ማለት ነው።

ይህ ካልሆነ ዛሬ የካፒታሊስት አልባን የእድገት ቅና በሚያራምዱ አገሮች ያለው ላእላይ መዋቅር በምን ይወሰናል ?

ምንም እንኳ በእነዚህ አገሮች በስልጣን ላይ በሬት የነበረው የፊውዳሉን የምርት ግንኙነት ወይንም ሥርአት የሚወክለው የዘውድ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የህግ፣ የገዳማዊያን፣ ወዘተ. ወገኖች የሚያስጠብቀው የገዥ መደብ ከሥልጣን ላይ ቢወርድም እንኳንድ የፊውዳሉን ሥርአት የሚያረጋግጡ ካፒታሊዝምን የሚያስከትሉ እርምጃዎች ቢወሰዱም በመሰረታዊ ለውጥ አላደረጋቸውም። በስልጣን ላይ የወጣው አሁኑ የጊዜ መደብ / የንኡስ ከበርቴው / ከዚህ በፊት የነበሩትን የምርት ግንኙነቶች ለሱ በሚመች መልክ አድርጎ ካለመሰረታዊ ለውጥ አስቀምጦ እንጂ፣ ፍጹም መሰረታዊ ቀይረው የኢኮኖሚውን እድገትም ሆነ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የ ህግ፣ ወዘተ. መሻሻል እንዲያረጋግጡ አድርጎ እርምጃ አልወሰደም። በተጨማሪም ዛሬ ባለው

ልዩ ክስተት (Phenomena) ማለትም የካፒታል ዓለም አቀፋዊነት፣ እነዚህ የካፒታሊስት ኢኮኖ እድገት ቀዳና ይከተላሉ የሚባሉ ሃገሮች እንደቀደሙት የአውሮፓ ከበርቴ ነጻና ተፈጻሚ ባለመሆናቸውና ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በሱ ቁጥጥር ስር በመውደቃቸው መሠረታዊ በወጠኑት ፈለግ ወደፊት መራመድ አልቻሉም፡፡ ማለትም በቁጥጥር ስር ያደረጋቸው ዓለም አቀፋዊ ካፒታል፣ እነዚህ አገሮች በውስን /የተወሰነ/ ለውጥ ብቻ እንዲረኩ /በዚያው እንዲቆሩ/ በልዩ ልዩ ሃረግ ተብትቦ ያዛቸው፡፡ ይህ እኛስ የገዢ መደብ የወሰዳቸው እርምጃዎች የፊውዳሊዝም ሥረ መሠረት ቢያናጉም ከፒታሊዝም እንዲስፋፋ በር ቢከፍቱም፣ እኛስ የምርት ግንኙነት / የምርት መሳሪያዎች ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል በመንግስት ቁጥጥር ስር መዋላቸው/ ከእኛስ ታዳጊ ክ ሆነ ኢኮኖሚ ጋር ወይንም የምርት ሃይል ጋር በተመጣጠነና ፈጣን ሁኔታ መጓዝ የማይችል በመሆኑና ዛሬ ባለው ልዩ ክስተት / የኢምፔሪያሊዝም መኖር / የምርት ሃይሎችን ባለበት እንዲረገጡ እንዳያድጉና በህብረተሰቡ ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ እንዳይመጡ አፍኖ ያዛቸው፡፡ በመሆኑም ይህ እኛስ የተፈጠረው የምርት ግንኙነት /ምርት ያለ ለውጥ በፊውዳሉ የኢኮኖሚና የባህል የፖለቲካ አውታሮች በፍጥነት የተተናኘው /የተያያዘው/፣ ሆኖም ግን ሥርአቱ በካፒታሊስት የእድገት ደረጃ ውስጥ ያለ ግን እየርቋዘ የሆነና ይህ የኢኮኖሚ ሥርአትን ቢቀል የፖለቲካ ሳእሳይ መቀቀርም የሱ ነጸብራቅ እንጂ፣ ካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ እንደሚለው የሶሻሊስት ፕሪስፕክቲቭና የባህል ና የኢኮኖሚ ሁኔታ አይወስኑትም ማለት ነው፡፡

1.3.1.1.1.1. የካፒታሊስት አልባ እድገት የሶሻሊስት ሥርአት፣ በአረጀውና አሮጌ የመንግስት መኪና ላይ በመመርኮዝ ሊመገንባት ይችላል ይላል፡፡

ይህ ቲዎሪ እንደሚለው፣

" The country's subsequent development...,quite apart from its transition to all-out construction of socialism and the triumph of the latter, can be achieved only as a result of fundmental changes in the class charachter of the state apparatus,...and its turning into a state of the working people." (19)

እስከአሁን እንደተመለከትነውና የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪ ደጋፊዎች እንዳረጋገጡልን፣ ይህን ጎዳና በሚከተሉ አገሮች በስልጣን ላይ የወጣው ራዲካል ንኡስ ከበርቴ መደብ ወደ ሶሻሊዝም እንደሚያመራና ሶሻሊዝምን እንደሚገነባ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሥልጣኑን በእንዳች አይነት መንገድ / አብዛኛውን ጊዜ በኩዴታ/ የጨበጠው ንኡስ ከበርቴ መደብ ከድሮው መንግስት የነጠቀውን የመጨቆኛ መኪና በመጠቀም፣ እሱን በመጠገን ለሰፊው ህዝብ ገልጋሎት ለማዋል ይችላል ይላል፡፡

ነገር ግን ህብረተሰብ በመደቦች ከተከፋፈለ ጊዜ አንስቶ መንግስት የሁሉን መደብ ጥቅም በእኩል እንደማያስጠብቅና፣ ሌላው ከሱ በታች ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ረግጦ ለመግዛት፣ የመጨቆኛ መሳሪያ እንዳገለገለው፣ ይህ የመጨቆኛ መሳሪያውና ቢሮክራሲው የሱ መገለገያ እንደነበረ ነው፡፡ የአረጀው ስርአት ሲደመሰስ ደግሞ፣ አዲሱ መንግስት በተለይም የወዝአደሩና የአርሶ አደሩን ጥቅም አስጠብቃለሁ የሚል፣ አዲስ ህብረተሰብ ሊመሰረት የሚችለው የአረጀውን ስቴት ማሽን በመጠቀም ባይሆን እሱን በመሰባበርና ሌላ አዲስና ህይወት ያለው ህዝባዊ መኪና በሱ መቃብር ላይ ሲተከ ብቻ ነው፡፡

ግን የገዢ ከበርቴው መደብ ሥልጣን በጨበጥም ቅሉ የአረጀውን የመንግስት መኪና ለመሰባበር የመደብ ፀባዩ ፍላጎት አይፈቅድለትም፣ ቻ እንዲሁ ስልጣን ላይ ወጥቶ ቢይዝም በፊትም የነበረው መንግስት በፈጠረው ስቴት ማሽነሪ እየተጣራ እየተባበረ ወደ ገዢውና የከበርቴው መደብ ጋር ለመጣጋት ከሌሎች ከበታች ካሉት መደቦች አራሱን ከፍ በማድረግ ለመታየት ይፈልጋል፡፡ ሌኒን እንደሚለው፣

" In particular it is precisely the petty-bourgeoisie that is attracted to the side of the big bourgeoisie and is subordinated to it to a larger extebt by means of this very apparatus, which providesthe upper sections of the peasentry, artisans and tradesman with a number of comparativly compfortable, quite and respectable jobs which raise their holders above the people."
(state and revolution page 35)

ስልጣን ከጨበጠ በኋላ ደግሞ በመጠገንና በማጠናከር ከአረጀው ቢሮክራሲ ጋር እየተቀየጠ፣ ህዝባዊ እንቅስቃሴያችን ማፈኛ ይጠቀምበታል፡፡ ዛሬ የካፒታሊስት አልባን የእድገት ጎዳናን ይከተላሉ በሚባለው አገሮችም የሚታየው ሀቅ ይሄ ነው፡፡

በመሆኑም፣ ቲዎሪው በድሮው የመንግስት መኪና ለህዝብ የሚያገለግል አዲስ መንግስት መመስረት ይቻላል ብሎ ከማመኑ የተነሳ፣ የአመጽ ትግልን ወሳኝነት አይቀበልም፡፡ እንዲያውም፣ ሰላማዊ የትግል መንገድን በዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ አንድ አንዱ የትግል አይርገው የሚመለከቱትን፣ ግን ደግሞ የመጨረሻ መጨረሻ ሥልጣን በታጠቀ የህዝብ አመጽ ላይ ተመርኩዞ ብቻ ሊመጣ ይችላል ብለው የሚያምኑትንና ለዚሁም የሚታገሉትን 'ግራ ቀዎ'ች ናቸው በማለት ይወነጅላል፡፡

ሆኖም ግን ማርክስ፣ ኤንግልስ፣ ሌኒን እንደሚያስተምሩንና በአብዮት ታሪክ ውስጥ ባገኘነው ልምድ እንዳረጋገጥነው፣ የወዝአደሩም መደብ ሆነ ሌሎች የተጨቆኑ መደቦች አፈናቸውን ነፃ ለማውጣት የትጥቅ ትግል ማካሄድ እንዳለባቸውና ሥልጣን ከጨበጡም በኋላ የወረሱትን መኪና መጠገን ባይሆን አሱን ደምጥማጡን ማጥፋት እንዳለባቸው ነው፡፡

ስለሆነም ይላል ሌኒን፣

"...it is clear that the liberation of the oppressed class is impossible not only without a violent revolution, but also without the distruction of the apparatus of state power, which was created by the ruling class and which is the embodiment of this alienation."

/ State and Revolution [illegible]

በተለይም በቅድመ ካፒታሊስትየእድገት ደረጃ ውስጥ የሚገኙ አገሮች ደግሞ፣ የገዢውን መደብ ለመጣልና ህዝባዊ መንግስት ለመመስረት፣ ትግሉ ቸል አስቸጋሪና ውስብስብ ይሆናል፡፡ እንደአንጻሩ ካልሆነና ጋይለኛ ህዝባዊ እንቅስቃሴ እየገፋ ካልመጣ በስተቀር

/ የኢትዮጵያን ሠራዊት/፣ በእነዚሁ አገሮች ያሉ ተራማጅ ሆኑ ሌሎች ጭቁን ህዝቦች የመደረጃትን የመንግሥት መብት ፍጹም የለ ነው፡፡ የመደረጃቸው ሆነ የቀሰተባው ጉዳይ በቁም ምስጢራዊ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የነጻነት ጀርነት ድጋፍ ረዳትና ወሰበሰበ ከመሆኑ የተነሳ፣ ሽለየን፣ ጨካን አቀረርጾ በራሱን ህዝብ የሚያቀናና ወደ መጨረሻ መጨረሻ ወደ ህዝባዊ ህሊና ሁኔታ ይወስነዋል ማለት ነው፡፡ የነጻነት የመውጫ ጉዳይ በዚያ አገር ያለው ተጨባጭ ተግር ነው እንጂ ሃቅ ነገር፣ ለሰራው ህዝብ ምንም ያህል ዉለቶች ቢተዓቹ ቀሉ የመጨረሻ መጨረሻ ሥልጣኑን በነፃ፣ በተደረጃ በታጠቀ የህዝብ አመጽ ደምስሶ ካልነጠቀ ወደ ነጻነት ለማምራት አንደማይችል ነው፡፡

የካፒታሊስት አልባ እድገት ጎዳ ወዘገበር ነዉ ብቻ ባይሆን የሚያናጉና ተብቀናው ለእውነተኛ ነጻነት ለሚሹ ለሚታገሉ ባይሆን ለንኡስ ከበርቴዎችና መበሰቻቸው የሆነ የፀረ–ማርክሲስት ቲዎሪ ነው፡፡

1.4. የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ 'ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ ነው' የሚለውንና 'የራስ በራስ መተማመንን' መርሕር አይቀበልም፡፡

ከላይ እንዳየነው፣ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ የነፃነትን የዉርጅትን የትግቀን ጉዳይ በፍጹም አይቀበልም፡፡ ከዚሁም በመነሳት ሰራው ህዝብ እየነቃ እየተደራጀና እየታጠቀ በአብዮቱ ውስጥ በመከረል የሚያደርገውን የታሪክ በራነቱን ማስመሰከር እንዳለበት አያመለክቱም በአንጻሩ ጎን፣ ታሪክ የሚሰሪው ሥልጣን በ ጠበቡ የቲት ንኡስከበርቴዎች ብቻ መሆኑን፣ እነ ዘሀ ንኡስ ከበርቴዎች 'ለአብዮቱ በሚያበዩት ቀንነትና ታማኝነት' የሰራው ህዝብ ነፃ መውጣት እንደሚወሰን አድርጎ ያቀርባል፡፡

አብዮትም ከተጨባጭ ሁኔታ ብቻ ባይሆን ከሰራው ህዝብ በተለይም ከነታው ከፍል አብዛኛው ለአብዮቱ ቀርጾ መነሳትንና ለዚህ መስዋእት እንደሚያስፈልገው አይገልጽም፡፡ አብዮት በዘረቀደ፣ ከሰራው ህዝብ ፍላጎት ወጪ፣ ከሰራው ህዝብ ተሳትፎና ከሰራው ህዝብ ቀስቀስ በኋላ ለመጣ እንደሚችል አያስረዳም፡፡ ባጭሩ ጭኮሪ ውስጥ ለውጥ፣ አብዮታዊ ለውጥ በንኡስ ከበርቴዎች ቻይነት እንደሚመጣ አድርጎ ያቀርባል፡፡

'የታሪክ ባለቤት ሰራው ህዝብ ነው፣ ታሪክንም የሚሰራው እሱ ነው' የሚለው መመሪያ በተጨባጭ ከመያወጡ የተነሳ፣ 'የራስን በራስ መተማመን' ይቃረራል፡፡ በመሆኑም ይላል ይሀ ቲዎሪ፣ የካፒታሊስት አልባ እድገት በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው በሶሻሊስት አገሮች 'አስፈላጊውን የማቴሪያል እርዳታ' ከለገሰቸው በኋላ ብቻ ይሆናል፡፡

እንደሚለንም፣

" The idea that the non-capitalist way of development only become possible thanks to the support of the socialist community..".

ከላይ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ እንዳመለከተልን፣ ይህንን ጉዳና የሚከተሉ አገሮች አብዮትን ለማካሄድ በእራሳቸው የመናወር ችሎታ፣ እራሳቸውን እራሳቸው ባይሆን ወደ ካፒታሊስት ያልሆነ እድገት ሊያሸጋግሩ የሚችሉት፣ ከሶሻሊስት አገሮች የሚገኘውን የማቴሪያልና የቴክኒክ እርዳታ ተገን ማድረግ እንዳለባቸውና ይህም ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡

ይሁንና፣ ታሪክን የሚሰራ ሰፊ ህዝብ ደግሞ በተደሚያ በራሱ መተማመን እንዳለበት፣ በራሱ የተማረ አብዮታዊ ኃይሎች፣ በመናወር ችሎታው በአገሪቱ ሀብት ላይ እምነቱን [illegible] እንዳለበት ከላለበዚያ ወደ እውነተኛው ነጻነት፣ የበልጽግና ጉዳና መሸጋገር በፍጹም [illegible]፡፡ ኪም ኢልሱንግ፣ " on the Dshutshe ideologie " በሚለው ጽሁፍ ውስጥ [illegible] ከላይ የጠቀስነውን መሰረታዊ አባባል ያረጋግጣሉ፡፡

" Revolution can never be imported or exported. Instead of us, the people of other countries could not bring the revolution into its consumation. The master of the revolution of a given land is the people it self and the decisive facter to bring about a succesful revolution is only if the people of that land relied on it self." (on the Dshutshe ideologie)

" የአንዱ አገር አብዮት ወደ ሌላ አገር እንደ ሸቀጥ የሚገባ አይደለም፡፡ እንደሸቀጥ፣ ከአንዱ አገር ወደ ሌላ አገር የሚላክም አይደለም፡፡ ደግሞ፣ እንደበዓን ኮሪያና የመሳሰሉ የሶሻሊስት አገሮች ቢኖሩም፣ የሌሎች አገር ህዝቦች አብዮታቸውን በነርሱ መናር ምክንያት ብቻ ከመጨረሻው ሊያደርሱት አይችሉም፡፡ የአንዱ የተወሰነ አገር አብዮት ፈጣሪዎችና አድራጊዎች፣ የራሱ የዚያው አገር ህዝቦች ናቸው፡፡ የተሳካ አብዮትን ለማከናወን ወሳኙ ጉዳይ የዚያ አገር ህዝቦች በራሳቸው መተማመናቸው ነው ". / ትርጉም የኛ/

ይሁንና ይህንን ደግሞ በሥራ ለማዋል፣ ኪም ኢል ሱንግ እንደሚለን፣ ትክክለኛ ርእዮተ ዓለም ያስፈልጋል፡፡ በትክክለኛና ባልተበረዘ ርእዮተ ዓለም ላይ ካልተመረኮዙ፣ በራስም ላይ ሆነ በሰራው ህዝብ ላይ እምነት ሊኖር አይችልም፡፡ በራሱና በሰራው ህዝብ ሀይሎች የሚተማመን፣ አብዮት ካለሰራው ህዝብ ሙሉ በሙሉ ተሳትፎ ወደ ተገባር ሊመነዘር አይቻልም በሉ፣ የሰራውን ህዝብ ወሳኝ ሚና በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚቀበል፣ ከላይ ኪም ኢልሱንግ እንደሚለን ትክክለኛ ርእዮተ ዓለም የሚከተል ፓርቲ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪ እንደሚለን የንኡስ ከበርቴው ፈቃል ባይሆን፣ በማርክሲስት ሌኒኒስት ርእዮተ ዓለም የሚመራ፣ የወዝአደሩ ፓርቲ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡

ሆኖም ነገ ራስ በራስ መተማመን ማለት ደግሞ፣ ፍጹም ከሌሎች አገሮች አብዮታዊ ለምዱ፣ ከተራማጅ አገሮች እርዳታ አያስፈልገም ማለት አይደለም፡፡ እውነተኛ እርዳታ በተለይም በአሁኑ የኢምፔሪያሊዝም ዘመን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን እርዳታ በጨው ግን እንደ ሆነ፣ ለማን እንደሚሰጥ ደግሞ፣ በበጨው ሃቀኛ ተራማጅነት በተቀበዩ ለእውነተኛ አብዮት መቶ ይወሰናል፡፡ ሰጨው ተራማጅ፣ ለሶሻሊዝም የቆመ ከሆነ፣ በምንም አይነት በሰው ሃገር ውስጥ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ አውታሮች ውስጥ ገብቶ አይፈተፍትም፡፡ ተቀባዩም እውነተኛ አብዮታዊ ከሆነ የእርዳታውን ወሳኝነት / ወሰንነት / በነገሪ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ የሚሊታሪ ሀ

ይዞታዎች ላይ የሚያመጣውን አዎንታዊ ሆነ አሉታዊ ውጤት በቅጡ ይመረምራል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም የበሬው ህዝብ 'በራስ መተማመን ወሳኝነት' 'የአርዓያ አጋዥነት' 'በሚያስከትሉ የተ ያያዙ ቢሆንም፣ የጋለኛው በምንም አይነት የመጀመሪያውን ሊተካው አይችልም፡፡

1.5 የካፒታሊስት አልባ እድገት አዲስ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቲዎሪ ነው

የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ እንዲያው በድፍናው የወጣ አይደለም፡፡ ወይ ገም ደግሞ ወደ ነጻነትና ወደ ዲሞክራሲ ለማምራት የሚታገሉ የሶስተኛ ዓለም ሃገሮችን ለመርዳት አዲስና ሌላ አማራጭ ቲዎሪ በመሆኑም አይደለም፡፡ የራሱ የሆነ መነሻና ስትራቴጂያዊ ግብ ያለው ቲዎሪ ነው፡፡ ይህ ቲዎሪ ባለፈው የተናታችን ክፍል ውስጥ ምን ያህል ፀረ-ማርክሲስት እንደሆነ፣ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ጋር ቀንደኛ ግንኙነት እንዳለው ልንረዳ ችለናል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ የዚህን ቲዎሪ መነሻና ስትራቴጂያዊ ግብ ባጭር ባጭሩ ለማየት እሞክራለሁ፡፡

ይህ ቲዎሪ መቼና ለምን ወጣ ?

ሃሳቡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጸነሰው፣ በሶቪየት ህብረት ከነበረው የሶሺዮ ኢኮኖሚ አቀማመጥ መቀየርና፣ የዶሮው የሶሻሊስት ፖለቲካዊ ሆነ ኢኮኖሚያዊ ደንቦች እየተጣሱ በሌላ እንዲተኩ መደረጉ ከጀመረ ወዲህ ነው፡፡ በ1956 ዓ.ም በሶቪየት የፖለቲካ መድረክ ላይ በዚያን ጊዜ ዘመናዊ ከላሽ በመባል የታወቀው ክፍልና የሪቪዥኒስቶችን፣ የቢሮክራቶችን ጥቅም ለማስከበርና የወዝአደሩንና የገበሬውን ጥቅም የሚጻረር ከሥልጣን ላይ ወጣ፡፡ የፖለቲካ ስልጣን የጨበጠ የገዥ መደብ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ይችላልና፣ በሥልጣን ላይ እንደወጣ የወዝአደሩንና የአርሶ አደሩን ተወካይ የነበረ፣ በበዙ መከራና ትግል ለሶሻሊዝም ግንባታ መስተዋጽኦ ያበረከቱ፣ በአዲሱ ከላሽ ቡድን ከቦታቸው እየተነሱ፣ በምትካቸው ደግሞ በየፋብሪካዎችና፣ በየህብረት አፀቫዎችና በሌሎች የወዝአደሩና የገበሬው የመታገያ መድረክ ላይ ከአዲሱ የገዥ መደብ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ ሪቪዥኒስቶችና የሥራ አስፈጻሚዎች ከወዝ አደሩና ከአርሶ አደሩ ፍላጎት ውጭ በጫንቃቸው ላይ ተጫኑ፡፡

በአጭሩ እንደዚሁ፣ ቀስ በቀስ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ህግ የሚጻረርና አዲሱን የገዥ መደብ፣ ቢሮክራቶችና ሪቪዥኒስቶችን ጥቅም በሚያስጠብቅ መንገድ እንዲቀየሩ እርምጃዎች ተወሰዱ፡፡ በአጠቃላይ ፕላን የሚመራው የሶቪየት ኢኮኖሚ፣ / የሶሻሊስት ኢኮኖሚን ከካፒታሊስት የሚለየው አንዱ መለኪያ /፣ ገባሽ በገባሽ የሚሆነው በሪቪዥኒስቶችና በቢሮክራቶች መሰብሰቡ በኢንዱስትሪዎች ላይ የበላይነት ተሰጣቸው፣ እንደ ቀላል ኢንዱስትሪዎች የወዝአደሩን የሌሎችን የህብረተሰብ ክፍሎች የማቴሪያልና የባህል ሁኔታ ለማሻሻል ባይሆን / የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ዋና ህግ /፣ ከትርፍ አንጻር ብቻ እንዲሰሩና ትርፍ የሚያመጡ ወይንም ደግሞ ለምርት ሥራ የወጣውን ዋጋ production cost) የሚመልሱ መዘጋት እንዳለባቸው / የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ዋና ህግ / በሚያደርጉ ደንቦች ተተኩ፡፡ በአጠቃላይ ወይንም ማእከላዊ ፕላን ፈንታ፣ በእያንዳንዱ የኢኮኖሚ ሴክተሮች፣ በየኢንዱስትሪዎች በተናጠል (decentralize) አቅዱ እንዲወጣ ተደረገ፡፡

ይህ የቀደመው የሶሻሊስት ህግ ተቀልብሶ በሌላ ከላይ እንደተመለከትነው መተካት የወዝ አደሩን መደብ ሌላ የበዝበዛ ሥርአት ውስጥ የከተተ ከሶሻሊስት የኢኮኖሚ ደንቦች ጋር የማይጣጣም እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

...ሶቪየት የሶሺዮ ኢኮኖሚ አቀማመጥ መቀየር በዘገታ ቢሆንም፣ ይህ የውስጥ ለውጥ ብቻ የአሁኑን የገዥ መደብ ትርፍ ለማካበት ሊያረካው አልቻለም፡፡ ስለዚህም ከውስጡ የሶሺዮ ኢኮኖሚ ጋር የሚስማማ አዲስ የውጭ ፖሊሲ መቀየስ ያስፈልገ ስለነበር፣ ሶቪየት ህብረት በዓለም አቀፍ የካፒታል ኮምፒቲሽንና የሥራ ክፍፍል እንድትገባ የሚያስችላት ፖሊሲ ታቅዶ ወጣ፡፡

በመሆኑም በአንድ በኩል ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር 'የሰላም ውድድር' (peaceful competition) የሚለውን ቲዎሪ በማውጣት በዓለም አቀፍ የውድድር መረብ ውስጥ ከተገባ፣ በሌላ በኩል በ1950 ዎቹ መጨረሻና በ1960 ዎቹ መጀመሪያ ላይ ከኮሎኒያሊዝም የጭቆና ቀንበር እየተላቀቁ በመውጣት ላይ የነበሩትን፣ የአፍሪካንና ሌሎች የሶስተኛ ዓለም አገሮች ወደ ኋላ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ውስጥ የሚገቡበትን ዘዴ ተለሙ፡፡ ስለዚህም በ1957 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ከዚያም ቀጥሎ በመስፋፋት በ1960 ዓ.ም. የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪ 'አዲሱና አማራጭ' የሶስተኛው ዓለም አገሮች 'ወደ ሶሻሊዝም ሊያመሩ' የሚችሉበት ቲዎሪ በሚል ወጣ፡፡

በዚህም አዲስ ቲዎሪ መሰረት፣ የመስፋፋት አላማዋን ወደ ተጠባቂ ለመነዘር፣ በመጀመሪያ ደረጃ በሷ ቁጥጥር ስር፣ የሷን ርእዮተ ዓለምና የፖለቲካ የሚያስተጋባ መንግስት ወይም ፓርቲ አስፈላጊ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው፣ በያዝነው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የተለያዩ የኢምፔሪያሊስት አገሮች አንዱ በኢኮኖሚ ደካማ የሆነ፣ በተፈጥሮ ሀብት ሀብታምና በስትራቴጂ አቀማመጥ አመቺ የሆነ አገር እንዳስፈለጋቸው ሰተት ብለው አያገኙም፡፡ በራሱና በበሬው ህዝብ እምነት የሌለው፣ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ፀረ-ኮሚኒስት መንግስት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህም ማለት፣ ኢምፔሪያሊስቶች ወደ ሶስተኛው ዓለም አገሮች ገብተው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሚሊታሪ ሄጀሞኒ ለመጠበቅ መሸጋገሪያ ድልድይ ማግኘት አለባቸው ማለት ነው፡፡

ሶቪየት ህብረትም ልክ እንደሌሎች ኢምፔሪያሊስት ሃገሮች በራሱና በህዝቡ የሚተማመን ሀቀኛ የወዝአደር ፓርቲ፣ ሶሻሊዝም የታመነ ባይሆን የፈለጋቸውንና የመረጧቸው /የሶሺዮ ኢኮኖሚ ነፃነታም አይፈቅዱላቸው/ አብዛኛውን ጊዜ እስከአሁንም በተግባር እንደታየው የንኡስ ከበርቴ መንግስት፣ ከሚሊታሪና የሲቪል ቢሮክራሲ ጋር ተባብሮ በበሬው ህዝብ ጫንቃ ላይ በመቀመጥ ፀረ-ዲሞክራሲን አገዛዝ ያሰፈነ ወይንም የሚያሰፍን ነው፡፡

ይህንን የመሸጋገሪያ ድልድይ ካገኙ በኋላና በተለይም ደግሞ ይህ መንግስት የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም የሚጻረሩ እርምጃዎች ከወሰደ ሶቪየት ህብረት ስርጎ የመግባት እድሏ የተሻለ ይሆናል፡፡ ዛሬ በሷ ቲዎሪ መሰረት ሁለት ብሎኮች አሉና /የሶቪየት የአሜሪካ የሆነ/ ከሁለቱ አንደኛውን እንዲመርጥ ለማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም፣ በዚህ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ መሰረት ይህንን አዲሱን ጎዳና አዲሱን ብሎክ የመረጡ፣ ከዚህ በፊት ከካፒታሊስት አገሮች ጋር የነበራቸውን የኢኮኖሚና የሚሊታሪ ግንኙነት ሰብረው 'ከሶሻሊስት ብሎክ' ጋር የጠበቀ ግንኙነት መመስረት አለባቸው፡፡ በመጀመሪያም በኢኮኖሚ ግንኙነት በኩል በሩ ያለ የልውውጥ መስክ መከፈት አስፈላጊ መሆኑን በይፋ ይናገራሉ፡፡

የሶቪየት ህብረትና ከኮሎኒያሊዝም ና ከኢምፔሪያሊዝም እየተላቀቁ የወጡትን ሃገሮች ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ምን ይመስላል ? በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ምን ውጤት አለው ?

ሶቪየት ህብረት በርጋ የመግባት እድል ካገኘች በኋላ / በእርግጥ በዚሁ በፈረደበት አለምአቀፋዊነት ስም ነው /፣ ከዚሁ በፊት በምእራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶች ተይዘው የነበሩትን የአገሩ ውስጥ ገበያዎች በሞኖፖሊ በራሷ ቁጥጥር ስር እንዲውል ታደርጋለች፡፡ ማለትም እነዚሁ አገሮች ከምሳ ኃይል የሶቪየትና ዋርሶ የሸቀጣሸቀጦች ማራገፊያ ይሆናሉ፡፡ በዚህም የውጭ ንግድ እንደቀደሞው ከአንዱ አቅጣጫ ተላቆ ወደ ሌላ አቅጣጫ በመዞር፣ እንደ ዱሮው ያልተመጣጠነ የንግድ ግንኙነት ይመሰረታል፡፡ ይህም 'አልሸሹም ዞር አሉ' ነው፡፡ ከአንዱ አየርጓዥ ወደ ሌላ አየርጓዥ መዞር ማለት ነው፡፡ አሁንም የንግድ አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ ወይንም አብዛኛውን ወደ አንድ አቅጣጫ ማምራት፣ የአገር ገበያ ከውጭ በሚመጣው ሸቀጣሸቀጥ መያዝ፣ የአገር ውስጥ ገበያ ሊስፋፋና የአገሪቱ ከበርቴ ከዚሁ ውድድር ተላቆ እያመረተ በነፃ ሊያድግ አይችልም፡፡

ይህ የሶስተኛው ዓለም አገር ገበያዎች፣ የውጭ ካፒታሊስቶች ሸቀጣሸቀጥ ማራገፊያ መሆን ደግሞ በሰው የመፍጠር ችሎታ፣ በገበያው አለመስፋፋት በሃገሬው ከበርቴ በምርት ሂደት ውስጥ በበቂ አለመሳተፍ፣ በጠቅላላው በአገር ኢኮኖሚ አስተዳደግ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ውጤት NEGATIVE EFFECT አለው፡፡ ስለዚህም ሶቪየት ህብረት ዛሬ በዓለም አቀፋዊነት ስም እነዚሁ ተራማጅ ወይንም ደግሞ የካፒታሊስት አልባን የእድገት ጎዳና ይከተላሉ የሚባሉ አገሮችን የምትጠጋቸው፣ በእርግጥም ከፊውዳል ኢኮኖሚ ተላቀው ነፃና በዘገታም በሆነ የሚያድግ ኢኮኖሚ እንዲያገኙና የህዝባቸውን ኑሮ እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ባይሆን፣ ከዚሁ በፊት የምእራብ ኢምፔሪያሊስቶች በሞኖፖሊ ይዘውትና እየተገለገሉ የሊቀቀትን ገበያ፣ የጥሬጥሬ ዕቃዎች(raw materials) በራሷ ቁጥጥር ስር ለማድረግና ለመዝረፍ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ / ለበለጠ ሬፈረንስ reference 'ታጠቅ' ሚያዝያ 1971 2.2.3. የውጭ ንግድ ችግር የሚለውን ተመልከት /

ይህ የሶቪየት ህብረት እሷሁ የእጅ አዙር ቀኝ ግዛት ቲዎሪ አንደኛው መልክ ነው፡፡

ሌላው የዚሁ የቀኝ ግዛት ቲዎሪና በተግባርም እንደሚታየው፣ ሶቪየት ህብረት የበላይነት ባላት ሀገሮች ውስጥ፣ እነዚሁ ሃገሮች በተወሰኑ የእርሻ ሰብሎች ላይ

culture)ብቻ አትኩሮ እንዲያደርጉና በዚሁ ብቻ እንደተሰለፉ ከዚያም ወደ ሶቪየትና ሌሎች የምስራቅ አውሮፓ አገሮች እንዲልኩ በልዩ ልዩ ዘዴ ተብትባ ይዛቸዋለች፡፡ ይህም የምእራብ ኢምፔሪያሊስቶች ከዚሁ በፊትና አሁንም የሶስተኛው ዓለም አገሮች በሞኖ ኩልቸር ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ከሚያደርጉት የተለየ ከሆነ ፖሊሲ በምንም የተለየ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ኪዩባን የወሰድን እንደሆነ የኢኮኖሚ ዋልታዋ ስኳር ነው፡፡ የተወሰነም ክፍ ለሶሻሊስ ከአለም ገበያ ዋጋ ዝቅተኛ በሆነ ታቀርባለች፡፡ እንዲሁም ኢትዮጵያን የወሰድን እንደሆነ በቡና ሰብል፣ በስኳር በበቆሎ ወዘተ. ላይ አትኩሮ እንድታደርግ እየተገፋፋች ነው፡፡ በርግጥ ኢትዮጵያ ከብዙ አመታት ጀምሮ ዋናው የኢኮኖሚ ዋልታና ከውጭ ንግድ ከምታገኘው ገቢ 60 ያህል የያዘው የቡና ሽያጭ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ሶቪየት ህብረት ልክ እንደ አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ኢትዮጵያ በዚሁ መስክ ላይ ብቻ አትኩሮ እንድታደርግ መገፋፋት ብቻ ባይሆን ባትወድ በግድ ተሸክማ ታደርጋለች፡፡

የአንድ ሃገር በተወሰኑ የእርሻ ሰብሎች ላይ አትኩሮ ማድረግ ምን አሉታዊ ውጤት አለው ? የዚሁን አሉታዊ መልክ እንደሚከተለው በጭሩ ለማስቀመጥ ይቻላል፡፡

1ኛ/ በማንኛውም ጊዜ ከሰው ቁጥር ውጭ፣ የእርሻ ሰብል፣ በጎርፍ ፣ በፀሐይ፣ በተባዮች፣ እንዲሁም በልዩ ልዩ የእርሻ ሰብል ህሞት ተበላሽቶ ምርት ሊቀንስ ይችላል በዚሁም ወደ ውጭ የሚላከው የተመነው ክፍም ሆነ ወይንም ውጉ በጣም ዝቅ ይላል፡፡ በአ

ከዚሁ የውጭውን ንግድ የሚመጣው ገቢ በጣም ይቀንሳል ማለት ነው፡፡

2ኛ/ 'ታጠቅ' እንደሚለከተው የእርሻ ውጤቶች ወይንም ጥሬጥሬዎች በኢንዱስትሪዎች ጋር ሲወዳደሩ ዋጋቸው በየጊዜው የሚቀያየር FLUCTUATE የሚያደርግና መሆኑ የንግዱ ሚዛን በየጊዜው ጤናማ አይሆንም ማለት ነው፡፡

ይህ በአጠቃላይ ጥሬጥሬ አቅራቢ የሆኑ አገሮችን የሚመለከትና በተለይም ደግሞ ወይንም በሁለት የእርሻ ሰብሎች ላይ ብቻ አትኩሮ የሚያደርጉ አገሮችን ምን ያህል ጎጂ በተዛባ መልክ ሊያድግ የሚችል መሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም፣ ሶቪየት ህብረት ዛሬ ይህንን 'የእድገት ጎዳና' ይከተላሉ የሚባሉ አገሮችን የጦር መሳሪያ ገበያ በሞኖፖሊ ይዛለች፡፡ እነዚሁ አገሮች የጦር መሳሪያ ስለሚገዙ / ኢኮኖሚያቸውም አይፈቅድም / በምልኩን ያሉ መንግስታት በሚከተሉት የተገኘነት ፖሊሲ አቅጣጫውን ከአንዱ ወደ ሌላ በመቀየር፣ ለጦር መሳሪያ መግዣ ለአመት በጀት ከሚያወጡት አብዛኛውን ለዚሁ ስለሚያፈሱ፣ ሌላውን የኢኮኖሚ ሴክተር ደንታ አይሰጡትም፡፡ ይህም ውስጥ በሚገባው መሳሪያ 1ኛ/ በምርት ሂደት ውስጥ ምንም ተሳትፎ ስለሌለው፣
2ኛ/ አብዛኛውን ጊዜ አዓውን በአይነት ስለሚከፈል፣ ቀስ በቀስ የኢኮኖሚው ጥገኝነት ወደ አንዱ አቅጣጫ መዞሩ ብቻ ባይሆን፣ እነዚሁ አገሮች ባይወዱ በግድ የኢኮኖሚ ጥገኛ ይሆናሉ፡፡ በተለይም፣ ዛሬ ሶቪየት ህብረት በገፍ ለምታቀርበው የጦር መሳሪያ እነዚህ የጦር መሳሪያ ማራገፊያ ብቻ ባይሆን ሰላም እንዳይደርስም የበጥበጣ ፖሊሲ ታካሂዳለች፡፡ ለዚህም ቀላል ነው፡፡ ጦርነት ሲኖር በየጊዜው የምታመርተውን የጦር መሳሪያ የመሸጥ እድል ከፍ ያለ ነው፡፡

ስለዚህም እነዚሁን አገሮች በቁጥጥሯ ስር ስማምጣትና በሃገሬ ነጻነታቸውን ለመግፈፍ / ገፉለች / የተበጸ ብህታዊ ሆና ትቀርባለች፡፡ ዛሬ እነዚሁ አገሮች እንደቀድሞው ገለልተኛ መሆናቸውን አቁመው አቅጣጫቸውን (መቀየር አለባቸው በማለት በድፍረት ትናገራለች፡፡

በጭም አባባል፡፡

" The foreign policy tenets and concepts which at one time served as a common platform for all third world countries now requires to be developed and defined more precisely. Positive neutrality and non-interference can no longer be interpreted as an effort to steer a course of balance between the two systems. Non capitalist developement is not possible on such a basis. It demands closer relation with the socialist community..." (20)

• የሶስተኛው ዓለም አገሮች ቀደም ሲል በውጭ ፖሊሲ ረገድ ይከተሉት የነበረው ፖሊሲና የጋራ መድረክ ባሁኑ ወቅት በአዲስ መቀየስና መታረም አለበት፡፡ ገለልተኝነትና በአንዱ አገር ውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፣ በሃያላን መንግስታት መካከል ሚዛንን የጠበቀ ፖሊሲ ለመከተል፣ እንደሚደረግ ጥረት ሆና መተርጎም የለበትም፡፡ እንደዚሁ ኢይነቱን ፖሊሲ በመከተል፣ የካፒታሊስት አልባ እድገትን ለማዓበር አይቻልም፡፡ የካፒታሊስት አልባ እድገት በተጨማሪ፣ ከሶሻሊስቱ ማህበረ ሰብ ጋር የጠበቀ ትስስርን ይጠይቃል፡፡ ' / 20 /

እንግዲህ በካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ መሰረትና በግልጽ ከላይ በዝርዝር እንደ ሚነገረን፣ የነገሩ ትርጉም እነዚህ አገሮች ብሄራዊ ነጻነታቸውን ሸጠው ሶቪየት ህብረትን ያስገቡ የሚል ነው፡፡ ለማንኛውም አንዱ ሃገር የራሷ ነጻና ጠንካራ ኢኮኖሚ ከሌላት ብሄራዊ ነጻነቷን ለማስከበር እንደማትችል በሁለቱ በኩል ያለውን ሶሻሊስቲካዊ ግንኙነት 'ታጠቅ' ሚያዝያ 1971 ትምህርታዊና ሳይንሳዊ ትንተና ሰለሰጠ፣ አልመለሰበትም 1፥3 'የኢኮኖሚ ስርአትና ብሄራዊ ነጻነት' የሚለውን ተመልከት፡፡

ይህ ከላይ የካፒታሊስት አልባ አድገት ያበረረው ደረር አቀረረብን ምን ያህል የሶቪየት ህብረት የሶስተኛውን ዓለም አገሮች በቀጥተኛ ስር ለማምጣትና የሄጌሞኒ ምትሃቷን ለማሟላት፣ እንዲሁም እነዚህን አገሮች እንዴት በንቀት እንደምትመለከት እንረዳለን፡፡

አንዱ ሃገር በተለይም በአሁኑ በኢምፔሪያሊዝም ዘመን በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ካለች፣ አብዮቷን እስከ ፍጻሜ ለማድረስ ይህ ትግል ከብሄራዊ ነጻነት ትግል ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆን አለበት፡፡ ይህንን የማይረዳ፣ በአብዮትና በብሄራዊ ልዕልና ነጻነት መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት የማይገነዘብ፣ በፍጹም ስለአብዮትና ተከታይም ስለ ሙሉ የኢኮኖሚ የበሸል እንዲሁም የባህል ለውጦች ቀንጣት አልተረዳም ማለት ነው፡፡ አንደኛውን ትቶ ለአንደኛው እታገላለሁ ማለት የሚሄድበትን የማያውቅ በአየር ላይ እንደሚንሳፈፍ ባሉን ነው ማለት ነው፡፡

1.6 ማጠቃለያ

በዚች አጭር ጥናት ውስጥ የካፒታሊስት አልባ አድገት ከታሪካዊ ቁስ አካል ጋር እንደሚጻረር፣ ከማርክስና ኤንግልስ እንዲሁም ሌኒን አባባል ጋር ለማወዳደር፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘቱን በየረድፉ በማስቀመጥ ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ጋር የማይጣጣም መሆኑን ለማሳየት ሞክሬአለሁ፡፡ ለማስታወስ ያህል ባጭር ባጭሩ ለማስቀመጥ እሞክራለሁ፡፡

1.0/ በዚህ ክፍል፣ የካፒታሊስት አልባ አድገት ቲዎሪ፣ ታሪካዊ ቁስ አካልን /HISTORICAL MATERIALISM/ እንዴት እንደሚጻረር፣ የህብረተሰብ አድገትም በዚህ ጎዳና ያላለፈና የማያልፍ መሆኑን ከማርክሲዝም አንጻር በማወዳደር የቲዎሪውን ስህተት ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

1.1/ በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ የማርክስና ኤንግልስ አባባል እንዴት እንደነበረና ከምን ተነስተው እዚህ ግምገማ ለመድረስ እንደቻሉና ይህም ምናልባታዊ ጉዳይ እንደሆነ፣ ይሁንና ደግሞ የሶሻሊስት አብዮት ካለወዛደሩ መደብ መሪነት ሊካሄድ እንደማይችል ማሳየታቸውን አመልክቻለሁ፡፡

1.1.1./ የሌኒን መነሻ ምን እንደሆነና፣ በካፒታሊዝም የእድገት ደረጃ ውስጥ ማለፍ አያስፈልጋቸውም ሲል ምን ማለቱ እንደሆነና እንዲሁም ይህ አቋሙ መነገዱ ምን እንደሆነና የራሱን የኢኮኖሚ ችግሮች መፍታት መቻል እንዳለበት፣ የራሱ የኢኮኖሚ ህጎች እንዳሉትና ይህንን ባያደርግ ካለበለዚያ ለሚተካው ህብረተሰብ የሚሆኑ የማቴሪያል ሁኔታዎችን ማዘጋጀት የማይችል መሆኑን አመልክቻለሁ፡፡

1.2./ እያንዳንዱ የህብረተሰብ ሥርአት የራሱ የተለዩ የኢኮኖሚ ህጎች እንደነበሩትና የአንደኛው በአንደኛው መገዛት እንደማይችል ስናረጋግጥ፣ የካፒታሊስት አልባ እ-ድገት ጎዳና ግን የራሱ የሆነ የኢኮኖሚ ህግ የሌለውት መሆኑን አሳይቻለሁ፡፡ የራሱ የሆነ

ኢኮኖሚ ህጎች የሉትና በሱ የማይተዳደር ከሆነ ደግሞ እንደዚህ አይነቱ ህብረተሰብ ሥር አይኖርም ማለት እንደሆነም ለመመልከት ችለናል፡፡

1.3/ የፖለቲካ ይዘቱን ስንመረምር፣ የካፒታሊስት አልባ አድገት ንኡስ ከበርቴውን መደብ የአብዮት መሪና በሬውን ህዝብ ወዛደሩንም ጭምር ነጻ ያወጣል ብሎ ስለሚያምን የንኡስ ከበርቴውን የመደብ ወስንነትና፣ የዲሞክራቲክ አብዮትን ከፍጻሜ አድርሶ ሶሻሊዝምን የሚገነባው የወዛደሩ መደብ ብቻ እንደሆነ አሳይተናል፡፡ በንኡስ ከበርቴው የሚመራው ሶሻሊዝም፣ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ሳይሆን የንኡስ ከበርቴው መሆኑን አሳይተናል፡፡

1.3.1./ በዚህ ክፍል፣ .. መንግስት ማለት ምን ማለት እንደሆነና መንግስት የሁሉን መደቦች ጥቅም ለማስጠበቅ እንደማይችል፣ ነገር ግን የወዛደሩ መደብ ሶሻሊዝምን ገንብቶና መደብ የሌለው ህብረተሰብ ለመሸጋገር ስለሚፈልግና በተፈጥሮ አብዮታዊ መደብ ስለሆነ፣ በዚህ በፊት የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችንም ጥቅም በመጠበቅ ነጻ የሚያወጣ መሆኑን አሳይተናል፡፡

1.3.1.1./በዲሞክራሲ ላይ ያለውን አሳይንሳዊ የሆነ አቀራረብና የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ መፈታት ምን ያህል ለኢኮኖሚና ለባህል አድገት እንዲሁም ለነፃነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውና ወሳኝም እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

1.3.1.1.1./ የላእላይ መዋቅሩ (political superstructure)

በሚመለከተው በኩል፣ ካፒታሊስት አድገት አልባ እንዳለን ባይሆን፣ ማርክስና ኤንግልስ እንዳሉትና እንዲሁም 'ታጠቅ' እንዳረጋገጠው የኢኮኖሚው ነጸብራቅ እንደሆነና ቅራኔያቸው ከኢኮኖሚው መሰረት የፈለቀ እንደሆነ አረጋግጠናል፡፡

1.3.1.1.1.1./የካፒታሊስት አልባ አድገት ያረጀውን ቢሮክራሲ ጠጋና እንዴት አዲስ ህብረተሰብ መፍጠር ይቻላል ብሎ እንደሚያምንና፣ ይህም ፀረ—ማርክሲስት እንደሆነ፣ የዲሞክራቲክ አብዮትን ከፍጻሜ ለማድረስና ሶሻሊዝምን ለመገንባት፣ በአረጀው መኪና ተጠቅሞ ሳይሆን፣ እሱን ሰባብሮ ብቻ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

1.4/ በዚህ ክፍል የካፒታሊስት አልባ አድገት 'ታሪክ ሰሪው ሰፊው ህዝብ ነው' የሚለውንና 'ራስን በራስ መቻል' እንዴት እንደሚጻረርና፣ በአንጻሩም የንኡስ ከበርቴውንና የሶሻሊስት ሃገሮችን ታሪክ ሰሪነት እንደሚያከብር ተመልክተናል፡፡

1.5./ በዚህ ክፍል የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ መቼና ከምን ጋር ተያይዞ [illegible] እንደሆነና አሰራሩም ምን እንደሆነ አዲስ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቲዎሪ እንደሆነና በኢኮኖሚ አድገት ያለውን እንቅፋት ባጭሩ አሳይተናል፡፡

በሚቀጥለው የጥናታችን ክፍል ደግሞ፣ የአሁኑን ዲሞክራቲክ አብዮት ታሪካዊ አመጣጥ፣ ለምን ዛሬ የሶስተኛ ዓለም አገሮች በዚህ ጎዳና መጓዝ እንዳለባቸው፣ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ይዘቱ ምን እንደሚመስል ባጭሩ ለማሳየት እንሞክራለን፡፡

2.0. የአሁኑ ዲሞክራቲክ አብዮት ታሪካዊ አመጣጥ

ዛሬ አዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት በመባል የታወቀው ጽንሰ ሃሳብ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መሰረቱ የተጣለው በማርክስ፣ ጀርመን በ1848 ዓ.ም. በከበርቴው አብዮት ውስጥ በምትገኝበት ወቅት፣ ቀጥሎ በሌኒን ራሽያ በ1905 ዓ.ም. በከበርቴው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ

በመትገኝበት ወቅት ነበር። በተለይም ሩሲያ በ1905 በቡርዧው አብዮት በነበረችበት ጊዜ በአንድ በኩል በሌኒን መሪነት በሩሲያ ሪቮሉሽነሪ ሶሻል ዴሞክራትና፣ በሌላ በኩል በሜንሼቪኮች በዚያን ጊዜ የቡርዧዊን አብዮት ማን ይምራው የሚለው ጥያቄ ላይ የመረረ ክርክር ተነስቶ ነበር። ሌኒንም አብዮታዊ እንቅስቃሴው የቡርዧው የሶሻል ፖለቲካና የኢኮኖሚ ጠባዮች እንዳሉት በማመን፣ ይሁንና የቡርዧው መደብ ቆራጥ ስላይደለ፣ ይህንን የዴሞክራቲክ አብዮት መርቶ ከፍጻሜው ሊያደርስ የሚችል ባይሆን፣ ወዝአደሩን ከመፍራቱ የተነሳ ከፀረ–አብዮት ኃይል ጋር ተሰልፎ የአብዮቱን ጊዜት ያጨናግፋል እያለ ይከራከር ነበር። ስለሆነም ወዝ አደሩ በሪቮሉሽናሪ ሶሻል ዴሞክራቶች ፓርቲ ስር በነጻ በመደራጀት፣ ይህንን የቡርዧ አብዮት ከፍጻሜ አድርሶ የሶሻሊስት አብዮት ለማካሄድ፣ አርሶ አደሩንና ሌሎች የአብዮት ኃይሎችን አስተባብሮ በመምራት የዴሞክራቲክ አብዮትን ማካሄድ አለበት እያለ ሲከራከር፣ ሜንሼቪኮች ግን የለም ይህ የቡርዧው አብዮት ነው፣ መካሄድም ያለበት በቡርዧው ነው፣ የሶሻሊስት አብዮት ብቻ ነው በወዝ አደሩ መካሄድ ያለበት እያሉ፣ ለቡርዧው ሽንጣቸውን ገትረው ይሟገቱ ነበር። ሆኖም ግን ሌኒን ይህንን የሜንሼቪኮች ሃሳብ ፉርሽ በማድረግ፣ የቡርዧውን ወላዋይነት አጋልጦ፣ ነገር ግን አርሶ አደሩ በንኡስ ከበርቴነቱ ወላዋይ ቢሆንም በሚደርስበት የፊውዳል ጭቆና የተነሳ የወዝ አደሩ አጋር እንደሚሆንና፣ በንጉሡም ላይ ወሳኝ ትግል ማካሄዱና ንጉሡንም መደምሰስ እንደሚያስፈልግ፣ ይህም ሌላ ሳይሆን የወዝ አደርና የገበሬውን አምባገነን መንግስት መመስረት ማለት እንደነበርና፣ ወዝአደሩ ለዴሞክራሲ ካለማቋረጥ እስከመጨረሻው የሚታገል መደብ ስለሆነ ከቡርዧው አመራሩን ለመንጠቅ መታገል እንዳለበት አስረዳ። የሚመሰረተውም መንግስት ሌኒን እራሱ እንዳለው የወዝ አደሩ አምባገነን መንግስት ሳይሆን፣ የዴሞክራቲክ አብዮት ስለሆነ፣ በወዝ አደሩ መሪነት የሚካሄድ የወዝአደሩና የገበሬው ዲክታተርሺፕ መሆን እንዳለበት አመለከተ።

ይህ ሌኒን ያሰፈረው መሰረታዊ ሃሳብ፣ በዚያን ጊዜ / 1905/ የአብዮታዊ እንቅስቃሴ ጠባይ የቡርዧው መሆኑን ይህንን አብዮት ከፍጻሜ ለማድረስ ወዝአደሩ ገበሬውን አጋሩ አድርጎ መታገልና መሪነቱን ከቡርዧው መደብ መንጠቅ እንዳለበት ና የሚመሰረተውም መንግስት የወዝ አደሩ አርሶ አደሩ ዲክቴተርሺፕ ነው የሚለው አስተሳሰብ፣ ዛሬ በማኦ ቤትንግ የዳበረውና አዲሱ ዴሞክራቲክ አብዮት በመባል የታወቀው ጽንሰ ሃሳብ ያስገኘልናል። አዲሱ የተባለውም፣ እንደ ቀድሞው በቡርዧው የሚመራና የቡርዧ የሚመሰርት ሳይሆን፣ በይዘት የቡርዧ ጠባይ ቢኖረውም፣ በወዝ አደሩ እየተመራና በአርሶ አደሩ አጋዥነት፣ በሌሎች የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ተባባሪነት ተመርኩዞ ስለሚመሰረትና የካፒታሊዝምን እድገት እስከተወሰነ ደረጃ ስለማይቃወም /አይችልም/ ነው።

2.1. / ከላይ የሰፈረውን ገለፃ በመመርኮዝ፣ የሶስተኛው አለም አገሮች በመባል የታወቁትን፣ ሶሻሊዝምን ለመገንባት ለምን በዚህ አዲሱ ዴሞክራቲክ አብዮት ውስጥ ማለፍ እንዳለባቸው በአጭሩ እንመልከት።

በያዝነው ኢምፔሪያሊዝም ዘመን፣ ማለትም ካፒታል ሃገር አቀፍ (national) መሆኑ ቀርቶ ዓለም አቀፍ መልክ እየያዘ በመምጣቱ፣ በከፊል ፊውዳል፣ በከፊል ከበርቴ ሥርአት ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች ካፒታሊዝምን በፍጥነት ሊያሳድጉት አልቻሉም። አይችሉም። ካፒታሊዝም እየተስፋፋ እንዲሁም የመጨረሻው ደረጃ ውስጥ ሲገባ /ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም/፣ እንደቀድሞው የኢንዱስትሪ ሸቀጣሸቀጦችን /ምርቶችን/ ብቻ ወደ ነዚህ አገሮች በመላክ ሊረካ አልቻለም። ይልቁንስ በቀጥታ የተወሰኑ ቀላልና የጥሬጥሬ ማውጫ የኢንዱስትሪ መኪናዎችን እየላከ እዚያው በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ምርትን እያመረተ የትርፍ ትርፍ (super-profit) መዛቁን ጥሩ ሆኖ አገኘው። ምክንያቱም እንደድሮው ጥሬጥሬዎችን(raw materials) ማጓጓዝ ስለማያስፈልገውና ርካሽ በመሆኑ፣ የጉልበት ሥራም ዋጋ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ የትርፍ ትርፍ ለማካበት አመቺ ሆኖ አገኘው። ወደነዚህ አገሮችም የሚላከው የምርት መሳሪያዎች

ለሱ ጥቅም ብቻ ተብለው ብቻ ስለነበር በህብረተሰቡ ውስጥ ይህን ያህልም ካፒታሊዝም በተሟላ መልክ እንዲያድግ አላደረገውም። ይልቁንስ፣ ይበልጥ መበዝበዝ ያስችለው ዘንድ፣ በተዘዋዋሪ በነዚህ አገሮች ባሉት መንግስታት ላይ ተጽእኖውን ማሳደር ጀመረ። በኢኮኖሚ በመጠኑም ቢሆን እየደገማቸው፣ ይበልጡኑ በመጨቆኛ መሳሪያቸው እንዲጠናከሩና ህዝባቸውን አረገጠው ለዘመናት እንዲገዙ በአማካሪነት፣ በአሰልጣኝነት ሰዎች እየላከ በአገሩ ውስጥም ከተማረው ክፍል ለሱ ጥቅም ያደረውን በጥቅም እያባለገ የፖለቲካ የበላይነት ተቀዳጀ። በሌላ ወገንም፣ የብሄራዊ ከበርቴው በአንድ በኩል፣ መንግስቱ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በመቆላለፉና ጭቆና ስለሚያደርግበት፣ በሌላ በኩል ጠንካራ ስላልነበረ፣ የታሪክ ተልእኮውን በማሟላት የቡርዧውን አብዮት በማካሄድ ካፒታሊዝምን በነጻ ማሳደግ አልተቻለውም። ኢምፔሪያሊዝምም በሚያካሂደው የመበዝበዝ ፖሊሲ፣ ካፒታሊዝም መልክ ባለው መንገድ ከማደግ ይልቅ፣ ለሱ ትርፍ ማካበቻ የሆነ የኢኮኖሚ መስኮች ብቻ እንዲጠገኑ ሲደረግ፣ የምርት ሃይሎችም በነጻ እንዳያድጉ አፍኖ ያዛቸው። ባጭሩ እነዚህ አገሮች ካፒታሊዝምን አሳድገው ወደ መጨረሻው የእድገት ደረጃ፣ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ሊሸጋገሩና በዚህም ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሰረት የሚሆኑ በምርት ሀይሎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድጉ ማድረግ አይችሉም።

ስለሆነም፣ እነዚህ በከፊል ፊውዳል፣ በከፊል ከበርቴ፣ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ውስጥ ያሉ ሃገሮች፣ ይህንን ውስብስብና አስቸጋሪ የእድገት ጉዳና ማለት ካፒታሊዝም አድጎ ሞኖፖሊ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ መጠበቅ የለባቸውም። በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታም አይችሉም። ስለዚህም መደረግ ያለበትና የሚቻለውም የዴሞክራቲክ አብዮት ነው ማለት ነው። የዚህ የዴሞክራቲክ አብዮት ደግሞ፣ ከላይ እንዳልነው፣ የብሄራዊ ከበርቴው የታሪክ ተልእኮውን ማሟላት የማይችል በመሆን ይህ ሃላፊነት በወዝ አደሩ ትከሻ ላይ ይወድቃል ማለት ነው። በነዚህ አገሮች የወዝ አደሩ ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም፣ በፓርቲው አማካይነት ተደራጅቶ አርሶ አደሩን አጋሩ በማድረግ፣ ሌሎች የዚህ በሬት የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን በግንባሩ ውስጥ እንዲሰለፉ አድርጎና አስተባብሮ፣ የዴሞክራቲክ አብዮትን መርቶ ከግቡ ለማድረስ የሚችለው ኃይል እሱ ብቻ ነው። ምክንያቱም ሌኒን እንዳለው፣

" only the prolstariat can be aconsistent fighter for democracy "
(Two tactics, page 61)

ይህም ማለት አርሶ አደሩም ሆነ / ንኡስ ከበርቴው እራሱ/ የንኡስ ከበርቴው መደብ እንዲሁም የብሄራዊ ከበርቴው ወላዋይ በመሆናቸው እስከ መጨረሻው ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ኃይሎች ስላልሆኑ የቡርዧውን አብዮት እየመሩ ከፍጻሜ አድርሰው ሶሻሊዝምን ለመገንባት ስለማይችሉ ነው።

ነገር ግን የዴሞክራቲክ አብዮት ወደ ፍጻሜ በወዝ አደሩ መሪነት የሚደርሰውን ያህል፣ አመራሩ በወዝ አደሩ ሳይሆን ይችላል። ይህም ማለት በንኡስ ከበርቴው ወይንም በብሄራዊ ከበርቴው ሊመራ ይችላል። ለምሳሌ የየካቲትን የኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ወደ ኋላ ዞር ብለን የተመለከትን እንደሆነ የእንቅስቃሴው ጀማሪ የንኡስ ከበርቴና መሪውም የንኡስ ከበርቴው መደብ አንደኛው ክፍል እንደነበር ነው። ይህ መደብ በተፈጥሮው ወላዋይ ስለሆነ አብዮቱን በቆራጥነት እየመራ ወደ ፊት መጓዝ አልቻለም። እንዲያውም፣ ዛሬ ደንታራ ሆኖ፣ ቢቀር እንኳ የካፒታሊዝምን እድገት 'እገታለሁ' እያለ እየተፍጨረጨረ ነው።

ይህም የሚያመለክተው በከፊል ፊውዳል፣ ከፊል ከበርቴ ስርአት ውስጥ የሚገኙ ወዝ አደሮች በቁጥር አነስተኛ ቢሆንም፣ የካፒታሊስት አሰባ እድገት ሊያወናብደን እንደሚገባው ሳይሆን፣ ንቅተው ተደራጅተውና ታጥቀው፣ ከሌሎች የተጨቆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተባብረው፣ የቡርዧውን አብዮት አካሂደው ፍጻሜ ለማድረስ፣ የታሪክ ተልእኮ በሌላ መደብ ሳይሆን፣ የግድ በነሱ ትከሻ ላይ ወድቋል ማለት ነው።

2.2/ የአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት መንግስት ምን ይመስላል ?

የአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት፣ ምንም እንኳ በወዝ አደሩ ይመራ እንጂ የዲሞክራሲ አብዮት እንደመሆኑ መጠን፣ የሚቋቋመው መንግስት የወዝ አደሩ አምባገነን ባይሆን፣ ሌኒን እንደሚለው የወዝ አደሩና የገበሬው አምባገነን መንግስት፣ ኋላም ግን እንደሚሰፋው፣ በወዝ አደሩ መሪነት ሌሎች የዘመኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ የሚሳተፉበት፣ ህዝባዊ ዲ.ቴተር ሺፕ (joint dictatorship of all revolutionary classes) ነው ማለት ነው:: በመሆኑም፣ ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም ፣ ፀረ- ቢሮክራቲክ ከበርቴ የሆኑ ሰፊ ኃይሎች በሙሉ የዲሞክራሲ መብቶችን ከሳጻች ገደብ በመቀዳጀት፣ የሚገፉበት ሃሳባቸውን በነጻ የሚያንሸራሽሩበት አዲስና ህይወት ያለው ዞ በመሰረቱ የሚያስፈጽሙን ዲሞክራሲያዊ መንግስት የሚገነቡበት ይሆናል ማለት ነው:: ምክንያቱም፣ የወዝአደሩ መደብ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተባትፍና መተባበር ፀረ- አብዮትን እየተከላከለ፣ የዲሞክራቲክ አብዮትን ማካሄድ ስለማይችልና ወዝአደሩ በአፈጻጸሩ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ኃይል እንደመሆኑ መጠን፣ ለራሱ ዲሞክራሲ ብቻ ባይሆን፣ ለሌሎች የዘመኑ የህብረተሰብ ክፍሎችም ጭምር የዲሞክራሲ መብቶቻቸውን ተቀዳጅተው በአስየቀ ውስጥ ተገቢ ቦታቸውን እንዲይዙ ያደርጋል::

የአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት ሊካሄድ የሚችለው ከአሮጌው መንግስት ላይ የተወረሰውን የመንግስት የመጨቆኛ መኪና መሰረት በማድረግ አይደለም:: ወይንም ደገምአሱን በመጠገን አይደለም:: የሚመሰረተው መንግስት፣ ህዝባዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ እንደመሆኑ መጠን፣ የድሮው የመንግስት መኪና ከነስረመሰረቱ ተደምስ በሱ መቃብር ላይ አዲስ ህዝባዊ የመንግስት መኪና ቦታውን ሲወስድ ብቻ ነው:: የድሮዉ የበሰበሰ ቢሮክራሲ መገልገያ የሆኑ ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ እስር ቤት፣ የስለላ ድርጅት .. ወዘተ. ከነስረመሰረታቸው ተገርስሰው በህዝባዊ መንግስት መገልገያ ማለት የፍርድ ሸንጎ፣ የፀጥታ ጥበቃ፣ ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት መተካት አለባቸው::

ይህንን የአዲሱን ዲሞክራሲ አብዮት ለማካሄድና ሥልጣን ጨብጦ ህዝባዊ መንግስት ለመመስረት ደግሞ፣ የጋዷታ ረጅምና ውስብስብ የጦር ትግል ማካሄድ ያስፈልጋል:: አዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት ከመሬት ተነስቶ አይካሄድም:: ወይንም የአረጀው መንግስት ስልቹ ተኛል ወይንም አርጅቻለሁ እንዘሁ፣ ስልጣን በቃኝ፣ ተረከቡኝ አይልም:: ይልቁንስ፣ ወዝ አደሩን በኢንዱስትሪ አምባዎች እያደራጁ አርሶአደሩን ደግሞ በገጠሩ ውስጥ እያደራጁና እያስታጠቁ የሁለቱን ትግል እያቀነባበሩና ማእከላዊ አመራር እየሰጡ ህዝባዊ ጦርነት ማካሄድ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም ሌኒን እንደሚለው የመጨረሻ መጨረሻ የፖለቲካን ነጻነት በኃይል ለመቀዳጀት ስለሚቻል ብቻ ነው:: በሱ አነጋገር፣

" In the final analysis force only settels the great problems of political liberty and the class strugle,...not only for defence but also for attack." (two tactics, page 30)

የነጻ የመውጣት ጉዳይ በዚያን ሃገር የዘበጥ ሀሳና ሁኔታ ይወሰናል:: ማለትም፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የቦሻል ሁኔታዎች ለአብዮቱ አመቺ ሆነው መገኘት፣ የወዝ አደሩ መደብ በፖርቲው አማካይነት መደራጀት መታጠቅ፣ የገበሬው መደራጀትና መታጠቅ፣ እንዲሁም ለአብዮቱ ሊሰለፉ የሚችሉ ቢያንስ የነቃው ክፍል ለአብዮቱ ዝግጁ መሆኑን፣ በአንፃሩም የፀረ-አብዮት ኃይሎች መዳከም ናቸው:: የትግሉም ረጅምነትና አጭርነትም እነዚህ በበረሩት መሰረታዊ ነገሮች ይወሰናል::

2.3. የአዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት ኢኮኖሚ

አዲሱ ዲሞክራሲ አብዮት በይዘት የከበርቴው አብዮት እንደመሆኑ መጠን፣ የካፒታሊዝምን እድገት አገታለሁ ብሎ ወይንም አሱን በመዝለል ሶሻሊዝምን አገነባለሁ ብሎ እንደ ካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ አይታገልም:: ይልቁንስ፣ ካፒታሊዝምን ባለመጻረር /አይችልም/ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ለሰፊው ህዝብ በሚጠቅም መልክ ቀይሶ ብሄራዊ ከበርቴው ለብሄራዊ ኢኮኖሚው እድገት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ፣ መንግስት እስከተወሰነ ደረጃ የግል ሀብትን ይፈቀዳል:: የብሄራዊ ከበርቴው በአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ዘመን፣ በጠቅላላው አንቀስቃሴ ውስጥ ያለውን ተባትፍ ካለምንም ስጋት የህዝቡን ጥቅም ሳይጻረርና ወዝ አደሩን ሳይጉዳ ከፍ እንዲያደርግ፣ መንግስት ዘመናዊ የአስተዳደር ዘዴ፣ ዘመናዊ የአካውንቲንግ አያያዝና የፋይናንስ አያያዝ ሪሾርስ የሆነ የጥሬዕቃ(raw materials) ጠቃሚ በሥራ ላይ እንዲያውል አስፈላጊውን እርዳታ ያደርግለታል:: በተጨማሪም ዘመናዊ መሳሪያዎችን በየጊዜው እንዲያሻሽል / በአዲስ እንዲተካ / ወይንም ሪሾርሳይዝ እንዲያደርግ ተለዋጭ የአቀራረብ ዘዴ ይጠቀማል:: መንግስትም የብሄራዊ ከበርቴው ኢንቬስት ማድረጉንና አለማድረጉን በየጊዜው ይቆጣጠራል::

ወዝ አደሩ የግል ሃብትን ወይንም ካፒታሊዝምን እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ እንዲያድግ የሚፈቅደው ህብረተሰቡ የቆመበትን የኢኮኖሚ ስርአት ጠንቅቆ የተረዳ በመሆኑና፣ እንደዚሁ ካፒታሊዝምን እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ እንዲያበጁና የሚረዱ እርምጃዎች እስካልተወሰደ ድረስ አዲሱን ዲሞክራቲክ አብዮት ገንብቶ ወደ ሶሻሊዝም ኢኮኖሚያዊም ሆነ ፖለቲካዊ መሰረት ለመጣል የማይችል መሆኑን ጠንቅቆ በመረዳቱ ነው::

ይህ የካፒታሊዝም መስፋፋት ወይንም አዳዲስና መጠነኛ ኢንዱስትሪዎች በግል እንዲቋቋሙ መፍቀዱ፣ በአንድ በኩል የሥራ መስኮች ሲከፍት ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል በዚህ አዳዲስበተከፈተው ኢንዱስትሪ እየተቀጠረ የሚገባው ወዝ አደር ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል:: በዚህ የወዝ አደሩ ወደፊት ለሚገነባው ሶሻሊዝም በቁጥር እየጨመረ፣ በፖለቲካ ንቃት እየዳበረ ከከበርቴው ጋር ለማይቀረው ሌላ የመደብ ትግል ፍልሚያ ይዘጋጃል:: ምክንያቱም ሶሻሊዝም በወዝ አደሩ የበላይነት ብቻ ስለሚገነባ ነው::

ከዚህ ሌላ፣ በዚህ በአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት መሰረት መሬት ለአራሹ የሚለው መፈክር በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል:: ከዚህ በፊት በጥቂት ባላባቶች እጅ ቁይዞ የነበረው በመወረሱ፣ ለድሃ ገበሬዎች እርሰው እንደጠቀሙበት ይታደላል:: በዚህም ገበሬው ከመሬቱ ለራሱ ተጠቅሞ የተረፈውን፣ ባይነጻ ለመንግስት በአይነት ቀረጥ (natural-tax)እንዲከፍል ቢደረግ፣ በተጨማሪም ለራሱ የሆኑ የቁጠባም ሆነ ለእርሻ የሚያገለግሉ የተሻሉ የምርት መሳሪያዎች በመግዛት በአንድ በኩል ኑሮውን እንዲያሻሽል ይረዳዋል:: በሌላ በኩልም ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴ እንዲጠቀምና የበለጠ ምርት እንዲያመርት ያስችለዋል::

በዚህም ከዚህ በፊት የነበረው የተፈጥሮ ኢኮኖሚ natural economy ገንዘብ (money economy)የተተካ ይበልጡኑ የገንዘብ እቃ ልውውጥ እየተስፋፋ፣ የአገሪቱ ገበያ ከውጭ ካፒታሊስቶች መዳፍ እየተላቀቀ ኢኮኖሚው በነጻ እንዲያድግ ይረዳል:: መንግስትም በዚህ የገንዘብ ኢኮኖሚ መስፋፋትና እራሱም ከገበሬው ከሚቀርበው ምርት በመጠቀም ካፒታል አከማችት (money capital) በማድረግ፣ ለመንገድ፣ ለመብራት፣ ለጤና ጣቢያዎች መስፋፋት፣ ለኢንዱስትሪዎችና ለመንግስት እርሻዎች መስፋፋትና ማደግ፣ በጠቅላላውም ለሶሻልና ለባህል እድገቶች የመዋለ ንዋይ (investment) ምንጭ ያገኛል ማለት ነው::

ሆኖም ገን ለአርሶ አደሩ የተለቀቀው መሬት በገሳዊነት እንዳይቀር መንግስት ቀስ በቀስ ገበሬዎች በህብረት እንዲያርሱ፣ በመጀመሪያ የስርቶ ማበያ መኪና በማዘጋጀትና በማሳየት፣ በገል ከማረስ ይልቅ ኮሌክቲቭ / በጋርዮሽ / ማረስ ምን ያህል ትርፍ እንዳለው

/ ጥቅም እንዳለው/ በጉልበት ባይሆን በዘዴና በትምህርታዊ መንገድ እያባበለው የህብረት እርሻ እንዲመሰረት ያደርጋል፡፡ መንግስት በሚወስደው የሰርቶ ማሳያ ሙከራ በህብረት እርሻና በግል መካከል ውድድር ይፈጠራል፡፡ የሰርቶ ማሳያው አጥጋቢና ፍሬያማ ከሆነ በሚፈጠረው ውድድር ከዚህ በፊት በግል ያርስ የነበረው ገበሬ ህብረት እርሻን መመስረት ይመርጣል፡፡ በተጨማሪም ገበሬው የፖለቲካ ንቃትና ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴን እንዲቀስም መንግስት ማንኛውንም ጥረት ስለሚያደርግ ህብረት እርሻን የመመስረት አዝማሚያው ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ይሄዳል፡፡ ይህ ደግሞ የራሱ የሆነ ሶሺያሊስቲካዊ እድገት አለው፣ በዘፈቀደ የሚመሰረት ባይሆን፣ ከፖለቲካና ከማቴሪያላዊ ለውጦች እድገቶች ጋር በቀጥታ የተሳሰረ ነው ማለት ነው፡፡

በሌላ ወገንም፣ በዚህ በአዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት መሰረት፣ ትላልቅ ኢንዱስትሪያች፣ ባንኮች፣ ትላልቅ የእርሻ ጣቢያዎች፣ ኢንሹራንስ / የጤና / የትራንስፖርትና የውጭ ንግድ በመንግስት ቁጥጥር ስር ሙሉ በሙሉ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ህብረተሰባዊ ጠባይ አላቸው ማለት ነው፡፡ መንግስትም እነዚህ እየተስፋፉና እያደጉ፣ በአዲስ እየተተኩና / በኢንዱስትሪ መኪናዎች/ ሆነ ትራንስፖርት ሲስተም / ለሰፊው ህዝብ ገልጋሎት እንዲውሉ በማእከላዊ ፕላን ይጠናቀራሉ ወይም ይከሄዳሉ፡፡

ከመጀመሪያው እንደጠቀስነው፣ የአዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግዜት የከበርቴው አብዮት አካል እንደመሆኑ መጠን፣ የሚተዳደረውም በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ህግ ባይሆን፣ በአሁኑ የከበርቴ ኢኮኖሚ ወይንም ቁጥጥር ስር የከበርቴ ኢኮኖሚ ህግ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ፣ አንዳንድ የከበርቴ ኢኮኖሚ ፈኖሜኖች መታየታቸው ስለማይቀር፣ እነዚህ ልዩ እንደቀድሞው የከበርቴ ኢኮኖሚ መሰን ለቀው እንዳይሄዱ መንግስት ቁጥጥር እያደረገ፣ የጠቅላላው የኢኮኖሚ እድገት ባይዛባ እንዲያድግ፣ መንግስት በየጊዜው አስፈላጊውን እርምጃ፣ ለምሳሌ የዋጋ ቁጥጥር፣ ወዛደሩ ከሥራ ቦታው እንዳይባረር፣ የወዛደሩ የሥራ መስክ እንዲሻሻል ወዘተ. ይወስዳል፡፡

የዚህ አዲሱ ከበርቴ ዴኢኮኖሚ በሥራ ላይ ማዋልና ለሶሻሊዝም መሰረት መጣል እንዲሁም ባይረበሽ መጠን በብዙ ሁኔታዎች ይወሰናል፡፡ አንዳንድ ሁኔታዎችን በነጠቀስ፣ የወዝ አደሩ ፓርቲ በሚከተለው ፖለቲካ፣ በሃገሪቱ የሚካሄደው እቅማመጥ፣ ከፍተኛ የተፈጥሮ አደጋ ከመጣ፣ በየጊዜው የሚታየው የአለም ተለዋዋጭ ሁኔታና በአካባቢው አገሮች ለሙጡ የሚችሉ ጦርነቶች፣ በአገሪቱ ውስጥ በየጊዜው ሊለዋወጥ የሚችለው የኃይል አሰላለፍ፣ የመጨረሻ ግን ደግሞ አስፈላጊ፣ ለአብዮቱ ሊሰለፉ የሚችሉ ኃይሎች በሙሉ በአላቸው አቅምና ችሎታ ለነጻ ኢኮኖሚ ግንባታ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰላም፣ አብሮ በመተባበርና በመፈታቀዱ አዲስ ህብረተሰብን ለመገንባት በሚያደርጉት ጥረቶች ይወሰናል፡፡

2.4. <u>ማጠቃለያ</u>

እስከ አሁን በቀረበው አጭር ጥናት፣ በካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪና በአዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ያሉትን፣ የቲዎሪ ልኑት ብቻ ባይሆን ወደ ተግባር የመመንዘርም ጉዳይ በመሃከላቸው ትልቅ ልዩነት እንዳለ ለመረዳት ችለናል፡፡

አንዳንድ መሰረታዊ ልዩነቶችን እንደገና ለማየት ይረዳን ዘንድ በማወዳደር እናቀርባለን፡፡

1/ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ የታሪክን ሂደት መገታት ወይንም መዝለል ይቻላል ቢል፣ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግን፣ የህብረተሰብን ህግ መገታት ወይንም መጣስ አይቻ

ለም፣ ይሁንናም በያች ባገኙት ልምድና በአሁኑ የኢምፔሪያሊዝም ዘመን ሊዘሉ የማይችሉትን የህብረተሰብ ደረጃ እየተቆጣጠሩና ለራሳቸው መጠቀሚያ እያደረጉ ለሶሻሊዝም መሰረት ሲጥሉ ይችላሉ ይላል፡፡

2/ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ፣ ካፒታሊዝም እንዳያድግ በገበያ አጠራት ቢልና ገን ደግሞ ካፒታሊዝም የሚያስፋፋውን እርምጃ ይወስዳ እያለ እርስ በራሳቸው የሚጋጩ ሃሳቦች ሲያቀርብ፣ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግን ግልጽና የማያወላዳ አቋም በመውሰድ፣ ተወደደም ተጠላም ካፒታሊዝምን መገታት አይቻልምና በቁጥጥር ካፒታሊዝም እየተዳደረ እድገና ተመናኮሬ ለሶሻሊዝም መሰረት አጥሳሰሁ በሉ አቋሙን ይናገራል፡፡

3/ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ ንኡስ ከበርቴው የአብዮቱ መሪ በመሆን ሶሻሊዝምን ሊገነባ ይችላል በማለትና ለንኡስ ከበርቴው ጥብቅና ሲቆም፣ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግን፣ ይህማ ስለ ንኡስ ከበርቴው ውስንነት አለማወቅ ብቻ ባይሆን በጠቅላላው ስለመደብ ጠባይ አለመገንዘብ ነው፣ ወዳጁ ማንኛውም መደብ ቢሆን ተመልሶ እራሱን አይወጋም፡፡ ስለዚህም በእራሱ አምሳል ዓለምን ለመለወጥ የሚታገለው ወዛደሩ፣ እሱ ብቻ ነው ብቸኛ ሶሻሊዝምን የሚገነባው ብሎ በግልጽ ያመለክተናል፡፡

4/ የካፒታሊስት አልባ እድገት ቲዎሪ በአረጀው ቢሮክራሲ አዲስ ህብረተሰብ መመስረት ይቻላል ቢል፣ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግን ይህማ ስለአብዮት ምንነት አለመረዳት ነው፣ አብዮት ማለት የመደብ ሹም ሽር ብቻ ባይሆን ከአሮጌው መንግስት የተወረሰውን የበሰበሰና ጉታች አድሃሪ የመንግስት መኪና ሰባብሮና አንኮታኩቶ በሱ መቃብር ላይ ህዝባዊ የመንግስት መኪና በቦታውን ሲወስድም ጭምር ነው በማለት ቁልጭ ባለ ቋንቋ ይነግረናል፡፡

5/ የካፒታሊስት አልባ ቲዎሪ አብዮት ማለት በመደቦች መሃከል የሚደረግ እርቅ አድርጎ ለማቅረብ ሞክርና ለንቃት ለደርሹት የሚደረገውን ጥረትና እንዲሁም የትጥቅ ትግል ሲያንቋሽሽ አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግን፣ ጭቁን ህዝቦች የመጨረሻ መጨረሻ ነጻነታቸውን የሚቀዳጁት በኃይል ብቻ ነው ብሎ በማያሻማ ቋንቋ ያስቀምጣል፡፡

Notes

1. V. Solodovnikov, Non-Capitalist Development page 24
2. MGE, SW Vol I page 504
3. R. Ulianovsky, Socialism & the newly independant nations, page 110
4. MGE, SW Vol II page 387
5. Ibid, page 392
6. Stalin, The foundation of Leninism, Peking edition page 2
7. Lenin, CW Vol 31 page 244
8. Ibid
9. MGE, SW Vol II page 403
10. V. Solodovnikov, Non-Capitalist Development page 101
11. R. Ulyanovsky, Socialism & the newly independant nations, page 64
12. Ibid page 76
13. " " 88
14. " " "
15. " " 73
16. " " 77
17. " " 102
18. MGE, SW Vol I page 503
19. R. Ulyanovsky, Socialism & the newly independant nations, page 100
20. Ibid page 66

በስዊድን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ለብሄራዊ ዴሞክራቲክ አብዮት

ለብሄራዊ ነፃነትና ክብር

ለአገር ወዳዶችና ለዴሞክራቶች ህብረት

ለሰፊው ሕዝብ ዴሞክራሲ

ለብሄረሰቦች እኩልነት

ለሴቶች የእኩልነት መብት

ሃቀኛ ተራማጆች ፣ ወዛደሮች ፣ አርሶ አደሮች ፣ አገር ወዳዶች ፣ ዴሞክራቶች የጭቁን ብሄረሰቦች ታጋዮች ፣ ምሁሮች ባለሞያዎች ፣ ወጣቶች ፣ ሴቶች ፣ ተራማጅ መለዮ ለባሾች ፣... ሕዝባዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት ተባበሩ።